# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 361 ጳጉሜን 1 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia







# የመሻገርን ድል አብሳሪ ፕሮጀክቶች

**ሄለን ወንድምነው**

ኢትዮጵያ የተፈጥሮ በረከት የተቸራቸው በርካታ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች አሏት፡፡ በየዘመኑ ባለው ትውልድ የተሠራና የተጻፈ ደማቅ የታሪክ ዐሻራም ተትረፍርፎባታል፡፡ ጊዜውን የዋጀና ገጽታዋን ከፍ ያደረገ ሰው ሠራሽ የቱሪስት መዳረሻዎችም ተገንብተዋል፡፡ ሕዝቡ በአንድነት ወጥቶ በአደባባይ የሚደምቅባቸው ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላትም በርከት ያሉ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ ያሏት ሃይማኖታዊና ባህላዊ የአደባባይ በዓላት፣ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ቦታዎች ለዕይታ እጅጉን ማራኪ ናቸው፡፡ የሰውን ቀልብ ይስባሉ፤ መንፈስን ያረካሉ፡፡ የዓለምን ትኩረት በመሳብ ተመራጭ የቱሪስት መዳረሻ ያደረጉም ናቸው፡፡


የመሻገርን ድል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## ኢንዱስትሪዎችን አሻጋሪው ኢትዮጵያ ታምርት

**ሄለን ወንድምነው**

ባለፉት ስድስት የለውጥ ዓመታት በኢንዱስትሪው፣ በግብርናው፣ በቱሪዝምና ሌሎች ዘርፎች አያሌ ሥራዎች ተከናውነዋል። ሥራዎቹ ኢትዮጵያን ያሻገሩና ማህበረሰቡን ተጠቃሚ ያደረጉ ናቸው።

በኢንዱስትሪው ዘርፍ ብቻ ከተከናወኑ


ኢንዱስትሪዎችን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# ዓባይ ግድብ-የኢትዮጵያ የመሻገር ትዕምርት

**ማርቆስ በላይ**



ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከሰሞኑ ስለ ግድቡ የሥራ ሂደትና አሁናዊ ቁመና በሰጡት ማብራሪያ፤ ህዳሴ መሻገር አይሆንላችሁም፤ ለእናንተ የተፈቀደና የተገባ አይደለም ላሉን ግለሰቦችና ቡድኖች ሕዝብና ሀገር ከወሰነ ምን ሊያመጣ እንደሚችል ማሳያ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ህዳሴ ከንግግር በላይ በመሆኑ ብዙዎች አይተው፣ ነክተው ካላወቁት በቀር ምን ያህል ግዙፍ ሥራ እንደሆነ መገንዘብ እንደማይችሉ ሲሉ ጠቅሰውም፤ ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በሃሳብ፣ በገንዘብ እና በጊዜ ብቻ እንዳልተገነባና በደም ጭምር የተገነባ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ በተለያየ ግንባር ተይዛ ሳለች 15 ሺህ የሚጠጉ የተለያዩ ቡድኖችን በህዳሴ ጉዳይ ተሠማርተዋል ያሉት ዐቢይ (ዶ/ር)፤ ሲሚንቶ ከማምረት ጀምሮ አጓጉዞ ቦታው ላይ እስኪደርስ የተለያየ ስም ያላቸው የተገዙ ሰዎች ሥራው አሁን ያለበት ደረጃ እንዳይደርስና እንዳይቋጭ ብዙ ጊዜ፣ ገንዘብና ሕይወት አጥፍተዋል ብለዋል፡፡

ላለፉት ሦስት ዓመታት ሲሚንቶን ከደርባ አንስቶ ህዳሴ ለማድረስ መከላከያ መንገድ እየጠገነ፣ ፈንጅ እየለቀመ፣ እየተዋጋ ግድቡ እንደተሠራ ጠቅሰው፤ ህዳሴን ብዙ ሰውተንበት፣ ደምተንበት፣ አልቅሰንበትና ደክመንበት ሠርተነዋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡


ዓባይ ግድብ-የኢትዮጵያ... ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory



Tel:- 0940 505050 – 0940 606060 – 0940 909090 – 0940 808080 -0920 656565



አቶ መሳኩ አለበል

## የአምራች ኢንዱስትሪዎች ዓመታዊ ዕድገት ወደ 10 ነጥብ አንድ በመቶ ከፍ ብሏል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት በወሰዳቸው የኢኮኖሚ ማሻሻያ የፖሊሲ ርምጃዎች የአምራች ኢንዱስትሪዎች ዓመታዊ ዕድገት ወደ 10 ነጥብ አንድ በመቶ ከፍ ያለ መሆኑን አቶ መላኩ አለበል ገለጹ።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የኢንቨስትመንት ፍሰትን ለማሳደግ የሚያስችል ውይይት ከባለድርሻ አካላት ጋር ትናንት አካሂደል።

በወቅቱ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል እንደገለጹት፤ የማክሮ ኢኮኖሚ ለውጦችን ጨምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተወሰዱ የፖሊሲ ማሻሻያዎች ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። በዚህም የአምራች ኢንዱስትሪ ዓመታዊ ዕድገት ወደ 10 ነጥብ አንድ በመቶ ከፍ ሊል ችሏል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ባለፉት ስድስት ዓመታት በኢትዮጵያ አምራች ኢንዱስትሪውን ለማሻሻልና በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን ለማድረግ በርካታ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል። ከዚህ ውስጥም የፖሊሲና አሠራር ሥርዓት ማሻሻያዎች ተደርገዋል።

በዘርፉ ትልቅ ለውጥ የሚያመጡ ውሳኔዎች የተወሰኑትም ባለፉት የለውጥ ዓመታት ውስጥ መሆኑን በማንሳት፤ በዚህም የኢንዱስትሪ ፖሊሲ፣ የግብርና፣ የፋይናንስና የኢኮኖሚ ሪፎርሞች፣ ለአምራች ዘርፉ አጋዥ የሆኑና ከዲጂታላይዜሽን ጋር የተያያዙ ውሳኔዎች ተወስነዋል ብለዋል።

ለአምራች ዘርፍ ከፍተኛ ሚና ያለው ከሎጀስቲክ ጋር ተያይዞ ያለው አገልግሎት የላቀ እንዲሆን መደረጉን አንስተው፤ የፋይናንስ አቅርቦቱን በተለይም ለአምራች ኢንዱስትሪው የተሻለ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ የለውጥ ሥራዎች በብሔራዊ ባንክ በኩል ሲሠሩ መቆየታቸውን አብራርተዋል።

የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለማድረግ የፖሊሲና አሠራር ማሻሻያዎች መደረጋቸውን ጠቅሰው፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተወሰዱ የኢንዱስትሪ፣ የግብርና፣ የፋይናንስና ዲጂታላይዜሽን ማሻሻያዎች ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ማነቆ የሆኑ ችግሮችን መፍታት እንደቻሉ አቶ መላኩ ገልጸዋል።

አቶ መላኩ፤ "ቀደም ሲል የማምረት አቅማችን ዝቅ ያለ ነበር። አሁን ላይ ከፍ ብሏል። በሀገር ውስጥ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ የነበረው የገበያ ድርሻ ዝቅ ያለ ነበር። ይህንንም ከፍ ለማድረግ ተችሏል" በማለት፤ እነዚህ በሙሉ ተደምረው የአምራች ኢንዱስትሪዎች ዓመታዊ ዕድገት ወደ 10 ነጥብ አንድ በመቶ ከፍ እንዲል ማስቻላቸውን አስገንዝበዋል።

በሁሉም ዘርፍ የተደረገው ሪፎርም በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ገብተው ለሚያለሙ ኢንቨስተሮች ምቹ ሁኔታን የፈጠረ መሆኑንም አስታውቀዋል።

የፖሊሲ ማሻሻያዎቹ በተለይም በሃይል አቅርቦት፣ በመሠረተ ልማትና በሎጀስቲክ ዘርፍ ይነሱ ለነበሩ ጥያቄዎች መልስ የሰጡ መሆናቸው ምርታማነትን መጨመር መቻላቸውንም ተናግረዋል።

# በተጠናቀቀው በጀት ዓመት በሁሉም የልማት ዘርፎች የተሳካ ሽግግር ተደርጓል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የተጠናቀቀው 2016 በጀት ዓመት በሁሉም የልማት ዘርፎች የተሳካ ሽግግር የተደረገበት ዓመት መሆኑን የፕላንና ልማት ሚኒስትር ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር) አስታወቁ። 230 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ እና ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ዋጋ ያላቸው ምርቶችን በሀገር ውስጥ ወደ ማምረት ሽግግር መደረጉን ጠቁመዋል።

ጳጉሜን አንድ የመሻገር ቀን ተብሎ የተወሰነ ሲሆን በዛሬው ዕለት ‹‹የመሻገር ጥሪቶች፤ የአዲስ ብርሃን ወረቶች›› በሚል መሪ ቃል ይከበራል።



ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር)

የፕላንና ልማት ሚኒስትር ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር) የመሻገር ቀንን አስመልክተው በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በግብርና፣ በአምራች ኢንዱስትሪ፣ በቱሪዝምና በኢነርጂ ዘርፎች ባለፉት ዓመታት በተተገበሩ ዕቅዶች የመሻገር ምልክቶች የታዩ በመሆኑ ጳጉሜ አንድ የመሻገር ቀን ተብሎ ተሰይሟል። መሻገር በአቅምና በማምረት አቅም የሚገለጽ ነው።

መሻገርን ለመግለጽ ዋናዎቹ ዘርፎች ግብርና፣ አምራች ኢንዱስትሪ፣ ቱሪዝምና የኢነርጅ መሠረተ ልማት ናቸው ያሉት ሚኒስትሯ፤ ግብርናን ለማዘመን፣ ከዝናብ ጥገኝነት ለማላቀቅ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። ሊለማ የሚችል ሰፊ መሬት፣ ትልቅ የውሃ ሀብትና አምራች የሰው ሃይል እያለ ላለፉት 60 ዓመታት ስንዴን ከውጭ ስናስገባ ቆይተናል ሲሉ አውስተዋል።

ዝናብ ተጠብቆ የሚመረት በመሆኑ የግብርና ውጤታማነቱ አነስተኛ እንደነበር አንስተው፤ በአሁኑ ጊዜ የአሠራር ባህልን በማሻሻል በስንዴ ራሳችንን ችለናል። እንዲሁም ለሌሎች ወደ ውጭ ለመላክ የፖሊሲ ለውጥ በማድረግ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ ከአራት ዓመታት በፊት አጠቃላይ የስንዴ ምርት ከ50 ሚሊዮን ኩንታል በታች ከነበረበት በዘንድሮው 230 ሚሊዮን ኩንታል ወደማምረት ሽግግር ተደርጓል። ይህ በምርት መጠንና በልምምድ መሻገርን ያመለክታል።

የተመረተው ከፍተኛ ምርት ስንዴን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ዕድል መፈጠሩን ያነሱት ሚኒስትሯ፤ የመንግሥት የመሥራት ባህልም መሻገሩን ያመለክታል። መሻገር የተቻለው እቅድ አቅዶ ተከታትሎና ደግፎ መፈጸም በመቻሉ ነው፤ ከመንግሥት የመፈጸም አቅም ጋር የሚሄድ ጉዳይ ነው ብለዋል።

በስንዴ ውጤት ማምጣት የተቻለው ስንዴን ለማምረት የሚያስፈልጉ ሥራዎች በመሠራታቸው ነው ያሉት ዶክተር ፍጹም፤ የመስኖ አቅምን የመጨመር ሥራ ተሠርቷል። እንዲሁም የኩታ ገጠም አሠራርን በመተግበርና የስንዴ ዘርን በምርምር በማሻሻል ለውጤት መብቃት መቻሉን ገልጸዋል። ይህም እስከ አንድ ቢሊዮን ዶላር ለስንዴ ግዥ ይወጣ የነበረውን ሙሉ ለሙሉ ማስቀረት የቻለ መሆኑን አብራርተዋል።

ሌላኛው ሽግግር የተሳካበት ዘርፍ የአምራች ኢንዱስትሪ ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ የፖሊሲ ለውጥ በማድረግ የወጭ ንግድን ማበረታታት ብቻ ሳይሆን ከውጭ ተገዝተው ወደ ሀገር የሚገቡ ምርቶችን መተካት የሚል ፖሊሲ ተግባራዊ ተደርጓል።አምራች ኢንዱስትሪው ወደማይመለስበት ዕድገት እየተሸጋገረ መሆኑ እየታየ ነው ነው ያሉት።

ከውጭ ቢገዙ ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ያወጡ የነበሩ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት የተቻለበት ዓመት መሆኑን ጠቁመው፤ ሙሉ በሙሉ ከውጭ ይገዙ የነበሩ ጨርቃጨርቅና የተለያዩ ምርቶችን በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ የሚያስችል የአቅም ሽግግር ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

ቆመው የነበሩ በርካታ ፋብሪካዎች ወደ ሥራ ገብተዋል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ከአራት ዓመት በፊት ወደ ሥራ የገቡ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከሶስት አይበልጡም፤ በአሁኑ ጊዜ 13 ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ ገብተዋል። ተጨማሪ ሶስት የሚሆኑ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ወደ ሥራ ገብተዋል። ከአምራች ኢንዱስትሪ አኳያ መሻገርን የሚያመላክት ትልቅ አቅም ስለመፈጠሩ አንዱ ማሳያ መሆኑን አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ በርካታ የታሪክና የባህል ሀብት አሏት የሚሉት ዶክተር ፍጹም፤ ባለፉት በርካታ ዓመታት ለመጠቀም የሚያስችል ኢንቨስትመንት አልነበረም። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች እምቅ የቱሪዝም ሀብቶችን ወደ እውነተኛ የቱሪስት መዳረሻነት የሚቀይሩ ኢንቨስትመንቶች መከናወናቸውን ገልጸዋል።

ሌላኛው በልማት መሻገርን የሚያሳየው የኢነርጂ መሰረተ ልማት ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ የህዳሴው ግድብ በርካታ ችግሮችን አልፎ ጥሩ ደረጃ ደርሷል። የሀገራት የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ አቅም ማሳያ የኢነርጅ አቅማቸውና መጠን ነው።ለኢንዱስትሪያልዜሽን እድገት ወሳኝ መነሻ የሚሆን የሃይል አቅርቦት በአስተማማኝ ሁኔታ ሊሰጥ የሚችል የህዳሴው ግድብ ተጠናቋል ሊባል በሚችል ላይ ደረጃ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

ግድቡ በያዝነው ዓመት ተጨማሪ ሁለት ተርባይኖችን በመጨመር አራት ተርባይኖች ሃይል እንዲያመነጩ የተደረገበት ጊዜ በመሆኑ የመሻገር ትልቁ ማሳያ ስለመሆኑ አመልክተዋል።

# የኢሬቻን በዓል ለማክበር ለሚመጡ ዲያስፖራዎች የማበረታቻ ጥቅሎች ተዘጋጅተዋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ሽመልሽ አብዲሳ ያቀረቡትን ጥሪ ተቀብለው የኢሬቻን በዓል ለማክበር ለሚመጡ ዲያስፖራዎች የማበረታቻ ጥቅሎች መዘጋጀታቸውን የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን አስታወቀ።

በኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ጽሕፈት ቤት የዲያስፖራ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ዳይሬክተር አቶ አሚን ጁንዲ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ፤ የፕሬዚዳንቱን ጥሪ ተቀብለው ኢሬቻን ለማክበር በርካታ ዲያስፖራዎች ይመጣሉ ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

ዲያስፖራዎቹ ከኢሬቻ በዓል ጎን ለጎን ከከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውይይት እንደሚያደርጉ ጠቅሰው፤ የሀገሪቱን የለውጥ ሥራዎችንና የቱሪዝም መዳረሻዎችን እንደሚጎበኙ ተናግረዋል።

መርሃግብሩ ላይ ለሚሳተፉ ዲያስፖራዎች በኢንቨስትመንት በኩል ከፍተኛ የሆነ ዕድል እንሚሰጥ እና ለኢሬቻ በዓል የተዘጋጁ የተለያዩ ጥቅሎችን እንዲያገኙ የሚያስችል ዝግጅት መደረጉን ጠቁመዋል።

በተለያዩ ዓለም ሀገራት የሚገኙ ዲያስፖራዎች ወደ ትውልድ ሀገራቸው በመምጣት የኢሬቻን በዓል ከኦሮሞ ሕዝብ ጋር ሊያከብሩ እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ኢሬቻ የኦሮሞን ሕዝብ የሚያስተሳስር እሴት መሆኑን ገልጸዋል።



አቶ አሚን ጁንዲ



ኮሚሽነር ሌሊሴ ዱጋ

የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽነር ሌሊሴ ዱጋ በበኩላቸው፤ ፕሬዚዳንት ሽመልስ አብዲሳ ለኢሬቻ በዓል ያቀረቡትን ጥሪ ተከትሎ ለሚመጡ ዲያስፖራዎች የአየር መንገድ ትኬት ቅናሽ ይደረጋል ሲሉ ገልጸዋል።

ባለፉት ጊዜ ዲያስፖራው ባለበት ሀገር ኢሬቻን ሲያከብር መቆየቱን ጠቅሰው፤ ጥሪውን ተቀብለው ለሚመጡ ዲያስፖራዎች የባሌ ተራሮች፣ ወንጪን ጨምሮ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ለማስጎብኘት ዝግጅት መደረጉን ጠቁመዋል።

ኢሬቻን ለመታደም ከሚመጡ ዲያስፖራዎች ጋር በልማት አጀንዳዎች ዙሪያ ውይይት እንደሚደረግ ጠቅሰው፤ በቱሪዝም ኢንቨስትመንት ለሚሠማሩ ባለሀብቶች ማበረታቻዎች መኖራቸውንም ተናግረዋል።

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ በዘንድሮው የኢሬቻ በዓል ላይ የኦሮሞ ዲያስፖራዎች እንዲሳተፉ ጥሪ ማቅረባቸው ይታወሳል።

# በሁለት ምዕራፍ የዲያስፖራ ጥሪ ከ22 ቢሊዮን ብር በላይ ወደ ኢኮኖሚው ፈሰስ ሆኗል

**ዳግማዊት አበበ**



አዲስ አበባ፡- በሁለት ምዕራፍ በተደረገ የዲያስፖራ ጥሪ 22 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ወደ ኢኮኖሚው ፈሰስ መደረጉን የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት አስታወቀ።

በኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት የማህበረሰብ ልማት ዳይሬክተር አቶ ነብዩ ሰለሞን እንደገለጹት፤ በሁለት ዙሮች በተደረጉ የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ጥሪ ከ100 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር ገብተዋል።

በዚህም ከ2014 እስከ 2015 ዓ.ም በተደረጉ የመጀመሪያው ሀገራዊ ጥሪ እና ከኢድ እስከ ኢድ ሀገራዊ ጥሪ 22 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ወደ ሀገሪቱ ኢኮኖሚ ፈሰስ ሁኗል ያሉት አቶ ነብዩ፤ ገቢው በፋይናንስ ተቋም የተጣራ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ነብዩ ገለጻ፤ ገቢው የአውሮፕላን ትኬት ከመግዛት፣ ከቪዛ አገልግሎት፣ ከሆቴል ወጪ፣ ከንግድ ሱቆች፣ ከኢንቨስትመንት እንዲሁም ለበጎ አድራጎት ሥራዎች ከዋሉ ወጪዎች የተገኘ ነው። ገቢውም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በተለይም የቱሪዝም ዘርፉን በእጅጉ አነቃቅቷል ሲሉ ገልጸዋል።

ሀገራዊ የዲያስፖራ ጥሪዎች ካስገኙት ኢኮኖሚያዊ አበርክቶ ባለፈ በርካታ ውጤቶች የተገኙበት ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በተለይም በ2014 ዓ.ም የተደረገው ሀገራዊ ጥሪ ትልቅ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ስኬት አስመዝግቧል ሲሉ ተናግረዋል።

በወቅቱ ከምዕራባውያን ይደርስ በነበረ ዲፕሎማሲያዊ ጫና 35ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባዔ እንዳይካሄድ ሙከራዎች ሲደረጉ መቆየታቸውን የሚያነሱት አቶ ነብዩ፤ መንግሥት በጊዜው እያደረገ ከነበረው የዲፕሎማሲ ሥራ በተጨማሪ ለዲያስፖራው ማህበረሰብ ሀገራዊ ጥሪ ንቅናቄ በማድረግና ሀገር ሰላም መሆኗን በማሳየት ጉባዔው እንዲካሄድ አድርጓል ብለዋል።

እንደ አቶ ነብዩ ገለጻ፤ ዲያስፖራው በሀገር ገፅታ ግንባታ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም። ኢትዮጵያ ካላት የዲያስፖራ ቁጥር አንፃር በልማት ተጠቃሚ እንድትሆን የሚያደርጋት ነው።

በሌላ በኩል ዲያስፖራው ማህበረሰብ የቴክኖሎጂ ሽግግር ከማምጣት፣ ባህልን ከማስተዋወቅ፣ ለሀገር አምባሳደር በመሆን እንዲሁም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከማሳደግ አንጻር ከፍተኛ ሚናን ይጫወታል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ አሁን የተደረገው ሶስተኛው ምዕራፍ ሀገራዊ ጥሪም ከኢኮኖሚ ፋይዳ ባለፈ በርካታ ስኬት የሚመዘገብበት እንደሚሆኑ ይጠበቃል ሲሉ አስረድተዋል።

አገልግሎቱ ከሶስተኛው ምዕራፍ የ2ኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ጥሪ ጋር በተያያዘ ከጳጉሜ 3 እስከ 5 ቀን 2016 ዓ.ም የሚቆይ "ጉዞ ወደ ሀገር ቤት የክረምት ፌስቲቫል" በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም እንደሚካሄድ ከሰሞኑ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ማስታወቁ ይታወቃል ።



# “ሠራዊቱ ተስፋፊዎችን መመከት የሚያስችል የተሟላ ወታደራዊ ቁመና ላይ ይገኛል”

## -ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- መከላከያ ሠራዊት የተስፋፊዎችን የጦርነት ነጋሪት ጉሸማ ለመመከት የሚያስችል የተሟላ ወታደራዊ ቁመና ላይ ይገኛል ሲሉ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ።

ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ትናንት በ47ኛው የምስራቅ ዕዝ ምሥረታ በዓል ላይ ባስተላለፉት መልዕክት፤ የእዙን የምሥረታ በዓል ከሰላም ወዳዱ የሶማሌ ሕዝብና ከጀግናው የእዙ አመራርና አባላት ጋር ለማክበር በመቻሌ ደስታ ተሰምቶኛል ብለዋል።

እእዙ ከምሥረታው ማግስት ጀምሮም ተስፋፊውን የዚያድ ባሬ ጦር ጨምሮ የተለያዩ የሽብር ሃይሎችን በመከላከልና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተሰጠውን ግዳጅ በጀግንነት ሲመክት የቆየ አንጋፋና ጀግና እዝ መሆኑንም አንስተዋል።

እዙ የዚያድ ባሬ ጦር ወደ መሀል ሀገር ያደረገውን ወረራ በመመከት መስዋዕትነት በመክፈል ጭምር የሀገሩን ዳር ድንበር እንዳስከበረ አስታውሰዋል።

የሀገርን ሰላም፣ ሉዓላዊነትና አንድነትን በማስጠበቅ ረገድ እዙ ከፍተኛ ዋጋ መክፈሉና የሠራዊቱ መመኪያ መሆኑን ገልጸው፤ ሠራዊቱ ሀገርን ለመውረር የሞከሩ ሃይሎች ለመመከት የሚያስችል ቁመና ላይ እንደሚገኝ አንስተዋል።

ኢትዮጵያን ለመውረር ግፊት ሲያደርጉና ግጭት ሲያባብሱ የነበሩ የሀገራችን ታሪካዊ ጠላቶች አብረው የቆሙ ቢመስሉም በሽንፈት ጊዜ እንደማይገኙ ከታሪክ መማር ይገባል ብለዋል።

ሠራዊቱ በቀጣናው ያለውን የተስፋፊዎች የጦርነት ነጋሪት ጉሸማ ለመመከት የሚያስችል የተሟላ ወታደራዊ ቁመና ላይ እንደሚገኝም ነው ፊልድ ማርሻሉ የገለጹት።

ውስጣዊ ችግሮች ቢኖሩም ሀገርን ከጥቃት ለመከላከል ብቻ ሳይሆን ከሞከሩ ዳግመኛ እንዳያስቡት አድርጎ ለመመከት የሚያስችል ዝግጁነት መኖሩንም ተናግረዋል።

በዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሠራዊቱ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ ማቅረባቸውን የመከላከያ ሠራዊት አስታውቋል።

ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ በምስራቅ እዝ የተገነባውን የገርባሳ አምፊ ቴአትር መርቀዋል። በመቀጠልም በሀረር ከተማ ተገኝተው የምስራቅ እዝን የ47 ዓመታት ጉዞ የሚዘክር ሙዚየምን ጎብኝተዋል።

በጉብኝቱ ላይ የጦር ሃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ምክትል ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ጀኔራል አበባው ታደሰና ጀኔራል ጌታቸው ጉዲናን ጨምሮ ከፍተኛ የሠራዊቱ አመራሮች፣ የሃይማኖት አባቶች እና የአካባቢው ማህበረሰብ ተገኝተዋል።

# በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከተከፈለው ግብር 83 በመቶ ያህሉ በፍቃደኝነት የተከፈለ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ከተከፈለው ግብር 83 በመቶ የሚሆነው በፍቃደኝነት የተከፈለ መሆኑን የገቢዎች ሚኒስቴር አስታወቀ።

በገቢዎች ሚኒስቴር የሰሜን ምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ከባለድርሻ አካላት እና ከግብር ከፋዮች ጋር በግብር አሰባሰብ ዙሪያ በትናንትናው ዕለት ተወያይቷል።

በወቅቱ ንግግር ያደረጉት በገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ አብዱራህማን ኢድ ጣሂር እንደገለፁት፤ እንደ ሀገር በፍቃደኝነት የሚሰበሰበው ግብር እየጨመረ መጥቷል። በ2016 በጀት ዓመት 83 በመቶ የሚሆነው ግብር በፍቃደኝነት የተከፈለ ነው።

በቀጣይም የግብር አከፋፈል ሥርዓቱ ምቹ እንዲሆን በቴክኖሎጂ በማዘመን የፍቃደኛ ግብር ከፋይ ዜጋ መጨመር ይገባል ብለዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ማህበረሰቡ ምን ያህል ግብር እንደተጣለበት ከማወቅ እስከ ክፍያ ያለው ሂደት በኤሌክትሮኒክስ የክፍያ አማራጭ በቤቱ ሆኖ እንዲከፍል የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቷል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ግብርን በአግባቡ በማይከፍሉ ነጋዴዎች ላይም የሕግ ማስከበር ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አንስተዋል።

የግብር ከፋይ አዲት የማድረግ አቅምን ለማሳደግ በትኩረት እየተሰራ መሆኑንም ተናግረዋል።

የሰሜን ምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ አቶ ኪሮስ ደበሱ በበኩላቸው፤ በጽህፈት ቤቱ በፍቃደኝነት ግብር የመክፈል ባህል እየተሻሻለ መጥቷል።

በ2016 በጀት ዓመት በጽህፈት ቤቱ 65 በመቶ የሚሆኑ ግብር ከፋዮች በፍቃደኝነት የከፈሉ መሆናቸውን ያነሱት አቶ ኪሮስ፤ የተቀረው ግብር በተደረገ የሕግ ማስከበር ሥራ የተከፈለ ነው ብለዋል።

በቀጣይ ፍቃደኝነት ግብር የሚከፍሉ ዜጎችን ቁጥር መጨመር ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ የሚገልጹት ሥራ አስኪያጁ፤ የሕግ ማስከበር ሥራውም በፍቃደኝነት ግብር የመክፈል ባህሉን የሚያበረታታ መሆን ይገባዋል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ኪሮስ ገለጻ፤ ለእቅዱ መሳካት ለግብር ከፋዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች በስፋት መከናወን ይኖርባቸዋል። የግብር ሥርዓቱን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ግብር ከፋዮች ባሉበት ሆነው ግብራቸውን መክፈል የሚችሉበት ኢ-ፋይል የተሰኘ ሥርዓት ተግባራዊ ተደርጓል። በዚህም 96 በመቶ የሚሆኑ ግብር ከፋዮች በሥርዓቱ እንዲከፍሉ መደረጉን ተናግረዋል።

# ኢንዱስትሪዎችን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ተግባራት የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ተጠቃሽ ነው። ንቅናቄው በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ መደረግ የጀመረው ከሚያዝያ 29 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን፤ ከ10 እስከ 15 ዓመት ድረስ ተግባራዊ ይደረጋል።

ንቅናቄው የኢትዮጵያን የማምረት አቅምና አጠቃቀም ለማሳደግ፣ የአምራች ዘርፍን ተግዳሮቶች ለመለየት፣ አዳዲስ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠርና የወጪ ንግድ ገቢን ለማሳደግ ዓላማ አድርጎ የተቀረፀ ነው።

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት ኃላፊ አያና ዘውዴ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት፤ ኢትዮጵያ ታምርት ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ዘላቂ ልማትና ተወዳዳሪነት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ሀገራዊ ንቅናቄ ነው።

የባለድርሻ አካላት ባለቤትነትን ማሳደግ፣ ለዘርፉ ምቹ የቢዝነስ ከባቢ መፍጠር፣ የአምራች ኢንዱስትሪ ግንባታ አመለካከትን ማሳደግ፣ የኢንዱስትሪያል ማህበረሰብ ግንባታ፣ የሀገር በቀል ምርቶችና አምራቾችን ማጠናከር እና መሪ ኢንዱስትሪዎችን መፍጠር የንቅናቄው ምሶሶዎች ናቸው።

አምራች ኢንዱስትሪው ለሀገር በቀሉ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ስኬትና የልማት ዕቅድ የታለመውን የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲወጣም ያስችላል ሲሉ ያስረዳሉ።

ንቅናቄው ከተጀመረ ጀምሮ የሕግና የአሠራር ሥርዓትን የማሻሻል፣ አደረጃጀትን የማሻሻል፣ የማስፈፀም አቅምን የመገንባት፣ ኢንቨስትመንት መሳብ፣ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አቅምን ማጎልበት፣ የማምረት አቅም አጠቃቀምን ማሳደግ፣ የአምራች ኢንዱስትሪ የወጪና ገቢ ምርቶችን ማሳደግ ተችሏል ይላሉ።

ዶክተር አያና እንደሚሉት፣ እንደ ሀገር የተጀመረው የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ተገቢውን የአመራር ትኩረት አግኝቶና በአደረጃጀት ተደግፎ ዘላቂነት ባለው መንገድ እየተሠራ ይገኛል።

ንቅናቄው በፌዴራል ደረጃ በስቲሪንግ ኮሚቴ እና በአምስት ካላስተሮች የሚመራ ሲሆን፤ በተዋረድም በየክልሎች የክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ አደረጃጀት ተፈጥሮ እየተሠራ ነው ይላሉ።

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ በዘርፉ ያሉትን እድሎች አሟጦ ለመጠቀምና ማነቆዎችን ለመፍታት አበረታች ውጤት እያስገኘ ነው የሚሉት ዶክተር አያና፤ የተቋማትን ቅንጅት በማጠናከር፣ የኢንዱስትሪዎችን ችግር በቅርበት በመፍታት፣ ምርት በማስተዋወቅና ዜጎች የሀገራቸውን ምርት እንዲጠቀሙ በማድረግ ተጨባጭ ውጤት እያስገኘ ነው። የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ከተጀመረ ጀምሮ በተደረጉ ድጋፎች 771 ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ እንዲመለሱ የተደረገ መሆኑን ይናገራሉ።

በተጨማሪም ከግብዓት፣ ከመሠረተ ልማት፣ ከሠለጠነ የሰው ሃይል አቅርቦት፣ የመሥሪያና የማስፋፊያ ቦታ ዝግጅትና ከጉምሩክ፣ ሎጀስቲክ አገልግሎት ጋር የተያያዙ ሁለት ሺህ 573 ችግሮች ተለይተው፤ አንድ ሺህ 890 መፍትሄ እንዲያገኙ ተደርጓል። በቀሪዎቹ 683 ላይ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

በሌላ በኩል 60 ሺህ 729 ነጥብ 19 ሄክታር ሳይት ፕላን የተዘጋጀለት መሬት ለኢንዱስትሪዎች መዘጋጀቱን ገልጸው፤ ከዚህ ውስጥ 24 ሺህ 833 ነጥብ 53 ሄክታሩ መሬት ከሶስተኛ ወገን ነፃ ሆኖ ለኢንዱስትሪዎች በመተላለፍ ላይ ይገኛል ይላሉ።

ንቅናቄው በፈጠረው መነሳሳት 865 የማምረቻ ማሳያና መሸጫ ህንጻዎች ተገንብተው፤ 772 አነስተኛና 459 መካከለኛ በጠቅላላው አንድ ሺህ 231 አምራች ኢንዱስትሪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉንም ይናገ ራሉ።

የአምራች ኢንዱስትሪ የኤክስፖርት እና ገቢ ምርቶች ማሳደግ ከውጭ ምንዛሬ ገቢ አንጻር በ2016 በጀት ዓመት ብቻ 290 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል። በተጨማሪም በ2016 በጀት ዓመት የተመረጡ 40 ምርቶችን በተኪ ምርት በማምረትና ወደ ሀገር ውስጥ ገበያ በማቅረብ ሁለት ነጥብ 84 ቢሊዮን ዶላር ማዳን ተችሏል።

ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ እንዲተኩ ከስትራቴጅ ቀረፃና የተለያዩ ድጋፎችና ክትትሎች በመደረጋቸው የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻ በ2015 በጀት ዓመት ከነበረበት 40 ነጥብ ስምንት በመቶ በ2016 በጀት ዓመት በሰባት ነትብ አራት በመቶ ማሳደግ መቻሉን ያስረዳሉ።

ከከፍተኛ የትምህርት እና የምርምር ተቋማት ጋር በመቀናጀት 167 የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ማከናወን ተችሏል የሚሉት ኃላፊው፤ 81 ያህሉ ወደ ተግባር ተቀይረዋል ይላሉ።

ኢንቨስትመንትን ከመሳብ አንጻር በተሠሩት ሥራዎች 179 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ አንድ ሺህ 119 አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን መሳብ ተችሏል። ከዚህ ውስጥ 220ዎቹ የውጭ ቀጥተኛ ናቸው ሲሉም ያብራራሉ።

በ2016 በጀት ዓመት አነስተኛና እና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ ሦስት ሺህ 262 እንዲቋቋሙ ተደርጓል። በዚሁ በጀት ዓመት ሰባት ሺህ 229 ኢንዱስትሪዎች ወደ ተለያዩ ደረጃዎች ተሸጋግረዋል። አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ፣ እና ኢንዱስትሪዎችን ከፍ ወዳለ ደረጃ በማሻገር ለ272 ሺህ 34 ዜጎች ቋሚ የሥራ እድል መፍጠር መቻሉን ያመላክታሉ።

ለዘርፉ በተሰጠው ትኩረት በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብቻ 13 ነጥብ 92 ሚሊዮን ቶን ግብዓት ቀርቧል። የፋይናንስ አቅርቦትንም ከማሻሻል አንጻር ለከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች 54 ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ደግሞ ስድስት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር ብድር ቀርቧል። የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትን በሚመለከት በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብቻ 503 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዶላር ማቅረብ መቻሉን ያብራራሉ።

በቀጣይም በለሙ የኢንዱስትሪ እና የአግሮ ፓርኮች ውስጥ የሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮችን ማሳደግ፣ ከውጭ የሚገቡ የአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት በተመረጡ የተወዳዳሪ ምርቶች እሴት ሰንሰለት ስትራቴጂ በመንደፍ ኢንቨስትመንት መሳብ ላይ ትኩረት እንደሚደረግ ያመላክታሉ።

የአምራች ኢንዱስትሪ የወጪ ንግድ ምርቶች ስብጥር ፣ ልማትና ግብይት ስትራቴጂ ኢንቨስትመንትን መሳብ፣ በገበያ ልማት፣ በኢንቨስትመንት፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና በአስተዳደር ክህሎት ላይ ያተኮረ የንግድ ልማት አገልግሎት ሥልጠናን ማሳደግ እና ሌሎች በርካታ ሥራዎች እንደሚከናወኑ ያስረዳሉ።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ለኢንዱስት ሪዎች የማምረት አቅም መሻገሪያ ድልድይ በመሆኑ፤ መንግሥትና ባለድርሻ አካላት ትኩረት ሰጥተው እንደሚሠሩ አጽንኦት ሰጥተዋል።

# ዓባይ ግድብ-የኢትዮጵያ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሥራው ወደመገባደጃው የደረሰው ግድቡ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያንን የማይሻገሩት የሚመስል ፈተና ጋርጦ የነበረ ትንግርታዊ የኃይል ምንጭ ነው። በተባበረ ክንድም ለስኬት በመብቃቱም ኢትዮጵያን ከጨለማ ወደ ብርሃን በማሻገር ላይ ይገኛል።

ይህን ሃሳብ የሚጋሩት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትር ዶክተር ኢንጅነር ሀብታሙ ኢተፋ፤ ኢትዮጵያውያን ህዳሴን በመጠቀም ከጨለማ ወደ ብርሃን እየተሸጋገርን እንገኛለን ይላሉ።

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ለኢትዮጵያውያን የአንድነት መለያ የሆነ ትልቁ ፕሮጀክት መሆኑን የሚገልጹት ሀብታሙ (ዶ/ር)፤ ህዳሴ ሲጀመር የዘመናት ቁጭቱ መልስ ያገኘ አድርጎ ሁሉም ከጫፍ ጫፍ ደስ ብሎት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያበረክት መቆየቱን ይገልጻሉ።

ግድቡ በመሃል ባጋጠመው የፕሮጀክት አመራር ቀውስ ምክንያት ህዳሴ ህዳሴን እንዳይሆን ተደርጎ እንደነበር ጠቅሰው የሞተ ፕሮጀክት ሆኖ መቆየቱን አብራርተዋል። በለውጡ ማግስት ፕሮጀክቱን ወደ ነበረበት ዓላማ ለመመለስ ማስተካከያና ርምጃ በመውሰድ ስኬታማ ተግባር መሠራቱን ይናገራሉ።

የኤሌክትሮ መካኒካል ሥራው ልምድ የሚጠይቅ በመሆኑ አቅምና ልምድ ያለው ተቋራጭ ማስገባት መቻሉ አንዱ ስኬት ነውም ይላሉ። መንግሥት ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ቅድሚያ በመስጠት የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሬ እና የሀገር ውስጥ ገንዘብ በማቅረብ ለፕሮጀክቱ ስኬት ትልቁን ድርሻ መወጣቱን ያብራራሉ።

ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ ህዳሴ ውጤት ማምጣት እንዲችል ማድረግ መቻሉን በመግለጽ፤ ውጤቱ ከፍተኛ የሆነ የሥራ ቁርጠኝነት፣ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ድጋፍ፣ የሚዲያዎችና ዲያስፖራዎች አስተዋጽኦ እንደነበረውም ያስረዳሉ።

ለግድቡ ኢትዮጵያውያን እናቶች ከሌለ መቀነታቸው ፈትተው የተቻላቸውን አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ጠቅሰው፤ በርካታ ዜጎች ሕይወታቸውን እንደገበሩበትም ይናገራሉ።

ህዳሴ በየዓመቱ ተጨባጭ ለውጦችን ያመጣ ሲሆን ከመጀመሪያ እስከ አራተኛ ዙር ውሃ ሙሊት መደረጉንና በሁለት ተርባይኖች 750 ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት መቻሉን ይገልፃሉ። በዘንድሮው ዓመትም ተጨማሪ ሁለት ተርባይኖች ወደ ሥራ በማስገባት ህዳሴ አንድ ሺህ 400 ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት መቻሉን ይገልጻሉ።

ህዳሴ ዝም ተብሎ አልተሠራም፤ የግድቡን መሠራት የማይፈልጉ አካላት በእጅ አዙር ኢትዮጵያውያን ደማቸው እንዲፈስ አድርገዋል የሚሉት ሚኒስትሩ፤ መኪና አሽከርካሪዎች፣ መከላከያና የፖሊስ አባላት ህዳሴ ዛሬ ለመድረሱ ስኬት ትልቅ ድርሻ አላቸው ሲሉ ያስረዳሉ።

ዛሬ ህዳሴ በሚያኮራ ሁኔታ ወደ ማይቀለበስ ትልቅ ስኬት ላይ መድረሱን ጠቅሰው፤ ህዳሴን በአሁኑ ትውልድ ወደ ተግባር፣ ተፈጻሚነትና ወደ ውጤት መቀየር የተቻለበት በመሆኑ መሻገር አርገን እናየዋለን ይላሉ።

ህዳሴ እንደ ሀገር መፈጸም ከማንችልበት ወደ ምንችልበት ደረጃ የመሸጋገራችን ምልክት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ በህዳሴ ዓባይን ይዘን መጠቀም ከማንችልበት ወደ ምንችልበት ማምጣታችን የመሻገር ምልክት ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

ህዳሴ ዛሬ አንድ ሺህ 400 ሜጋ ዋት ማምረት የሚችሉ አራት ተርባይኖች እንዳሉት ጠቅሰው፤ ህዳሴን በመጠቀም ከጨለማ ወደ ብርሃን እየተሸጋገርን እንገኛለን በማለት ይናገራሉ።

ህዳሴ ለኢትዮጵያውያን መሻገር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት በመግለጽ፤ ብዙ ሕዝብ ጨለማ ከነበረበት ወደ ብርሃን መሻገር የሚችልበት እንደሆነም ይገልጻሉ።

ለኢትዮጵያዊውያን አንድነት መገለጫ የሆነው ህዳሴ ሁሉንም ኢትዮጵያውያን ከጫፍ ጫፍ ማሳተፉን ገልጸው፤ በቀጣይም በአንድነት መቆም ከቻልን መፈጸም የማንችለው እንደሌለ ህዳሴ ማሳያ ነው ሲሉ ይናገራሉ።

ከለውጡ ወዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ ሲያጋጥሙ የነበሩ የሰላም እጦቶች፣ በተለያየ መንገድ የሚሠሩ ሴራዎች ከህዳሴ ፕሮጀክት ጋር እንደሚያያዙ የገለጹት ኢንጂነር ሀብታሙ፤ በህዳሴው የታዩ ፈተናዎች ለመሻገር በአንድነት መቆም ስለተቻለ ለስኬት መብቃት መቻሉን ያስረዳሉ።

ህዳሴ የዜጎችን ሕይወት ለማሻሻል አንዱ ትልቁ መሠረት በመሆኑ ሰዎችን ከድህነት ወደ ተሻለ ሕይወት፣ ወደ ብልጽግና ሊያሻግር እንደሚችልም ይገልጻሉ።

ከሚጠበቀው 74 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ለመድረስ ከስምንት ቢሊዮን ሜትር ኩብ ያነሰ የውሃ መጠን እንደሚቀረው በመግለጽ፤ አካባቢው ከፍተኛ የዓሣ ርባታ፣ የቱሪስት መዳረሻ፣ መጓጓዣ አገልግሎት ለመስጠት እንደሚያስችል ያመላክታሉ።

በርካታ ኢትዮጵያውያን ግድብን መምራት፣ መሥራት ምን እንደሆነ ከህዳሴ ልምድ እንደተገኘበት ጠቅሰው፤ ህዳሴ ለኢትዮጵያውያን አንድነት መገለጫነት አልፎ ለታችኛው ተፋሰስ ሀገራትም በረከት መሆኑን ይናገራሉ።

የሕዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ምክትል ዳይሬክተር ፍቅርተ ታምር፤ ህዳሴ በርካታ ችግሮችን በመሻገር ለውጤት የበቃ የኢትዮጵያውያን ፕሮጀክት መሆኑን ይናገራሉ።

ግድቡን አይገድቡትም፣ አይሠሩትም ስንባል ሠርተናል። ጫናዎችን በመቋቋም፣ በመሃል የደረሰበት የፕሮጀክ አስተዳደር ችግር ታርሞ ለውጤት በቅቷል ያሉት ምክትል ዳይሬክተሯ፤ ህዳሴ እውቀት፣ አቅም፣ አመራር፣ የማስተባበርና የመተባበር ተግባራት ተጣምረው የተገለጡበት ፕሮጀክት መሆኑን ይገልጻሉ።

በህዳሴ ግድብ አጋጥመው የነበሩ የፕሮጀክት ጥራት፣ አስተዳደር ችግሮችና አፈጻጸሞች ተፈትሸው ማስተካከያ እንደተደረገባቸው ጠቅሰው፤ ህዳሴ ያለበት ደረጃ እንዲደርስ መንግሥት ውሳኔ በማሳለፍ፣ አደረጃጀቱን የመቀየር፣ የመከታተል፣ የመደገፍና የማስተባበር ሥራ መሠራቱን ያስረዳሉ።

የፕሮጀክቱ ችግር በህብረተሰቡም ዘንድ ቁጣን ያስነሳና አመኔታውን ያጣበትና አልቆ ኃይል ማመንጨት ደረጃ ይደረሳል የሚል እሳቤም እንዳልነበር በመግለጽ፤ ባጋጠሙ ችግሮች ህብረተሰቡ በባለቤትነት ስሜት ይቆጣ እንደነበርና የለውጡ መንግሥት የወሰደው ርምጃ የሕዝብን ጥያቄ የመለሰ እንደነበር ይገልጻሉ።

ፕሮጀክቱ በተደረገለት ማስተካከያ ከነበረበት ችግር ወጥቶ ወደ ውሃ መያዝ ብሎም ኃይል ማመንጨት መሸጋገሩን የሚገልጹት ወይዘሮ ፍቅርተ፤ በግድቡ የተገኘው ውጤት ለሌሎች ሀገራዊ የልማት ሥራዎች ስንቅ በመሆን የሚያሻግር ነው ሲሉ ይናገራሉ።

በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የገንዘብ፣ የጉልበት፣ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ድጋፍ ማድረጋቸውን ጠቅሰው፤ ግድቡን አስመልክቶ የዲፕሎማሲ ጫናዎች ሲደርሱ ከመንግሥት ጎን በመሆን ፍትሃዊነትንና የጋራ ተጠቃሚነትን ማንጸባረቃቸውን ያስረዳሉ።

# የመሻገርን ድል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ከተቸሯት ተፈጥሯዊ ቦታዎችና በትውልድ ቅብብሎሽ ከቀጠሉ ታሪካዊ ቦታዎች በተጨማሪ ዘመኑን በሚመጥን መልኩ በርካታ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን እያለማች ነው። በአስደናቂ ታሪኳ በተለያዩ መልከዓ ምድሮች እና በውብ ባህሏ የጉዞ መዳረሻ ሆና እንድትቀጥል በቱሪዝም መሠረተ ልማት እየደመቀች ትገኛለች።

ባለፉት የለውጥ ዓመታት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሃሳብ አመንጪነት “ገበታ ለሸገር”፣ “ገበታ ለሀገር” እና “ገበታ ለትውልድ” የተሰኙ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ ገብተዋል።

በ“ገበታ ለሸገር” ፕሮጀክት አንድነት፣ ወዳጅነትና እንጦጦ ፓርኮች፣ የወንዝ ዳርቻዎችንና የመንገድ አካፋዮችን የማልማት፣ አረንጓዴ የማልበስ እና የሌሎች ፕሮጀክቶች ሥራ አካቶ ይዞ ተገብቷል።

በ“ገበታ ለሀገር” ከአዲስ አበባ ውጪ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮይሻና ሀላላ ኬላ፣ ከአማራ ክልል ጎርጎራ፣ ከኦሮሚያ ክልል ወንጪን እና በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ሌሎች ፕሮጀክቶችን ያለማ ፕሮጀክት ነው።

በ“ገበታ ለትውልድ” ደግሞ ስምንት ተጨማሪ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን ለማልማት ታቅዶ ግንባታ ቸው እየተካሄደ ነው። ፕሮጀክቱ በትግራይ ክልል ገራ አልታ፣ በአማራ ክልል ሀይቅ፣ በኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ በደቡብ ክልል አርባ ምንጭ፣ በአፋርና በሶማሊ ክልሎች ላይ እየተተገበረ ይገኛል።

በዚሁ ፕሮጀክት በቤኔሻንጉል ጉሙዝ ክልል በዓባይ ግድብ አካባቢ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻ ቦታዎች በባለሀብቶች እንዲለሙ ተደርጓል።

“የገበታ ፕሮጀክቶች” መገንባት የሀገሪቱን ገጽታ በእጅጉ ቀይሯል። ለበርካቶችም የሥራ ዕድል በመፍጠር እንጀራ ሆኗል። ለሀገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገትም ጉልህ ሚና አበርክቷል። ኢትዮጵያን ተመራጭ የቱሪስት መዳረሻ በማድረግም እንዲሁ።

የፕሮጀክቶቹ በአጭር ጊዜና በጥራት መገንባት የይቻላል መንፈስን በመላ ኢትዮጵያውያን አሳድረዋል። የኢትዮጵያን የተትረፈረፉ ሀብቶችንም አመላክተዋል። በቀጣይ ሌሎች ግዙፍ ፕሮጀክቶችንም ለማከናወን መንገድ ጠርገዋል።

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ እንደ ሚሉት፤ ባለፉት የለውጥ ዓመታት በ“ገበታ ለሸገር”፣ በ“ገበታ ለሀገር” እና በ“ገበታ ለትውልድ” በተሰኙ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን ማልማት ተችሏል።

በ“ገበታ ለሸገር” እና በ“ገበታ ለሀገር” ፕሮጀክት የለሙት የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ተጠናቀው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል የሚሉት አቶ ስለሺ፤ በ“ገበታ ለትውልድ” ፕሮጀክት ደግሞ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ተጨማሪ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን የማልማት ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ ያስረዳሉ።

አውሮፕላን ማረፊያ በሌለባቸው የቱሪስት መዳረሻ አካባቢዎች ትንንሽ አውሮፕላኖችን የሚያሳርፍ እና የተለያዩ መሠረተ ልማቶችን የማሟላት ሥራ መከናወኑን ይናገራሉ።

የፕሮጀክቶቹ መገንባት የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኚዎችን ቁጥር ለመጨመርና የቆይታ ጊዜያቸውን ለማራዘም፣ የውጭ ምንዛሬ ገቢን ለማሳደግ፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ማህበራዊ መስተጋብርን ለማጠናከር፣ የሀገሪቱን ገጽታ ለመገንባት እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የቱሪስት መዳረሻ ቦታ ባለቤት እንድትሆን ማስቻሉን ያብራራሉ።

የቱሪስት መዳረሻዎች ከማስተዋወቅ አንጻር በሀገር ውስጥ እና ከዚህ በፊት ተቋርጦ በነበረው በጀርመን፣ በእንግሊዝ እና በተለያዩ የዓለም ሀገራት በቱሪዝም ሚኒስቴር እና በግሉ ዘርፍ በኩል የማስተዋወቅ ስራ ተሠርቷል ይላሉ።

የሀገሪቱን የቱሪስት ቦታዎች በሀገር ውስጥ ሚዲያዎች ከማስተዋወቅ ባለፈም የብራዚል፣ የሩሲያ፣ የቻይና እና የሌሎች ሀገራት ሚዲያዎች እንዲጎበኙና እንዲያስተዋውቁ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል። የቢዝነስ ለቢዝነስ ትስስሮች፣ ኤግዚቪሽኖችን እና ሌሎች የማስተዋወቂያ ፕሮግራሞች መከናወናቸውንም ያመላ ክታሉ።

ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ከምትታወቅባቸው በተጨ ማሪ በርካታ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎች ስላሏት አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ብቻ ተንጠልጥሎ የነበረውን የቱሪዝም ገበያ ወደ አፍሪካ ለማምጣት በትኩረት እየተሠራ ስለመሆኑ ያስረዳሉ።

የተሠራው ሥራ የቱሪዝም ሥራ መዳረሻን ማስፋፋትና ሀገር ማስተዋወቅ ብቻ አይደለም የሚሉት አቶ ስለሺ፤ የቱሪስቶችን ፍላጎት በማሟላት የቆይታ ጊዜያቸውን ለማራዘም እና ወደ ኢትዮጵያ ለመሳብ ጥረት እየተደረገ ነው ይላሉ።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከማስተዋወቅና ከመዳረሻ ልማት በተጨማሪ “የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት” የቱሪዝም መረጃ የሚያዝበት ሥርዓት (ሲስተም) የበለጸገ ሲሆን፤ በመስከረም አጋማሽ 2017 ዓ.ም ለሕዝብ ይፋ እንደሚሆን ያመላክታሉ።

መንግሥት ለቱሪዝም ዘርፉ በሰጠው ትኩረት ከአምስቱ የሀገር በቀል የሪፎርም አጀንዳዎች ውስጥ በማካተት ዘርፉን ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን በመግለጽ፤ የተለያዩ የሕግ ማሻሻያዎችን የማድረግ፣ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን በመቅረጽ የመተግበር፣ የከተሞችን የቱሪዝም ብራንድ የማዘጋጀት፣ በዘርፉ የግሉን ሴክተርና የውጭ ባለሀብቶችን ኢንቨስት እንዲያደርጉ የማበረታት ሥራ ስለመሠራቱ ያስረዳሉ።

ላለፉት ዓመታት የሆቴሎች የጥራት የኮከብ ደረጃ ምደባ ሲከናወን መቆየቱን አስታውሰው፤ አሁን ላይ በሀገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የደግም የሆቴሎች የጥራት የኮከብ ደረጃ ምደባ ተከናውኗል። ውጤታቸው በቅርብ ይፋ የሚደረግ ሲሆን፤ የአገልግሎት ጥራትን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል ይላሉ።

በአጠቃላይ በሀገሪቱ በፊት ከነበሩት እጥፍ የሚሆኑ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች የለሙ ሲሆን፤ የቱሪዝም ቦታዎች የማስተዋወቅ ሥራን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጠይቀዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የመሻገር ተስፋችን በእጅ ፤ በደጃችን ነው!

እኛ ኢትዮጵያውያን ብዙ እያስከፈለን ካለው ድህነት እና ኋላቀርነት ወጥተን ሰላም እና ልማት መገለጫዋ የሆነች ሀገር ለመፍጠር በየዘመኑ በብዙ መነቃቃት ተንቀሳቅሰናል። እነዚህን መነቃቃቶች በአግባቡ መረዳት እና ለነሱ የሚሆን ማህበረሰባዊ መሠረት መጣል ባለመቻላችን ትናንቶቻችንን ተሻግረን ብሩህ የሆኑ ነገዎቻችንን መጨበጥ ሳንችል ቀርተናል።

ከትናንት የትልቅነት ትርክታችን የሚመነጨው ፤ሁሌም ነገን በቁጭት ብሩህ አድርጎ የማየት እና ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነት የመፍጠር ማህበረሰባዊ መነቃቃታችን፣ በያንዳንዱ ትውልድ ውስጥ "ትልቅ ነበርን፣ ትልቅ እንሆናለን" ከሚል የትናንት የታላቅነት የገዘፈ ታሪክ ምእራፍ ውስጥ የሚቀዳ እና በትውልዶች የማንነት ስሪት ውስጥ ጎልቶ የሚደመጥ ነው።

እንደ ሀገር በዚህ ከትናንት የመሻገር ማህበረሰባዊ መነቃቃት ውስጥ ያላለፈ ትውልድ የለም፤ እያንዳንዱ ትውልድ በዘመኑ የአስተሳሰብ መሠረት ላይ ሆኖ የተረዳውን፤ እንደየዘመኑ ዘመኑን ይዋጃል ያለውን አስቦ ለተግባራዊነቱ ብዙ ዋጋ ከፍሏል። የተከፈለውን ያህል ፍሬ ባያፈራም በየዘመኑ የተከፈሉ ዋጋዎች ዛሬ ላይ ያለው ትውልድ በተሻለ የመሻገር የታሪክ ምእራፍ ላይ እንዲገኝ የተሻለ እድል ፈጥረውለታል።

ይህ ትውልድ በተጨባጭ ከቀደሙት ትውልዶች በተሻለ ከትናንት የመሻገር እድል የተፈጠረለት ነው። ዓለም አቀፋዊና ሀገራዊ እውነታዎችን በአግባቡ ማጤን፤ ህልሞቹን ታሳቢ አድርጎ በበጎ ህሊናና እና በቅንነት መመላለስ ከቻለ የመሻገር ህልሙን እውን ለማድረግ የቀደሙ ትውልዶች በተፈተኑባቸው ፈተናዎች ተፈትኖ የሚወድቅበት ክፍተት ጠባብ ነው።

ትውልዱ አሁናዊ የእውቀት መገለጡን፣ ከአባቶቹ ቅንነትን፣ አርቆ አሳቢነትን፣ አብሮ የመኖር ሆደ ሰፊነትን፤ የሀገር ፍቅርን እና ብሄራዊ ክብርን ተምሮና ደምሮ መራመድ ከቻለ ፤ ብዙ ትውልዶች በብዙ ተመኝተውት ሳይጭብጡት ከሩቅ ሆነው የተሰናበቱትን ማህበረሰባዊ መሻትን እውን አድርጎ አዲስ ሀገራዊ ትርክት ለመፍጠር የተሻለ በሚባል የታሪክ ምእራፍ ላይ ነው።

በለውጡ ዋዜማ እንደ ሀገር የተጀመረው የለውጥ /የመለወጥ መነቃቃት የዚህ እውነታ ማሳያ ነው። በወቅቱ በሕዝባችን ላይ የታየው የለውጥ መነሳሳት በመሠረታዊነት ከትናንቶች የመውጣት እና ብሩህ ነገዎችን እውን የማድረግ እና ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነት ነው። ከትናንቶች የሚጠቅመውን ወስዶ ከማይጠቅሙት ጋር የመፋታት መነሳሳት ነው።

ከትናንት መፋታት ከትናንቶች ጋር ለረጅም ዘመናት አብሮ ከመኖር ጋር ከሚፈጠር መልመድ ጋር ተያይዞ በቀላሉ የሚከወን፤ ለራስ ብዙ ጊዜ ሰጥቶ ማሰላሰልን፤ በራስ ፍላጎት ላይ መጨከንን ለዚህ የሚሆን የመረዳት ቅንነትን የሚጠይቅ ነው። ከሁሉም በላይ ከራስ ወጥቶ ለማህበረሰብ የመሻገር ፍላጎት መሞትን የሚጠይቅ ነው።

የቀደሙት የለውጥ ታሪኮቻችን፣ የለውጥ መነሳሳቶቻችንን በተለወጠ ማንነት፤ በጠራ እውቀትና የመዳረሻ መንገድ ባለመገራታቸው ብዙ ዋጋ አስከፍለውናል። በግለሰቦች እና በቡድኖች መካከል የተፈጠሩ ትርጉም አልባ አተካራዎች፤ የሥልጣን መሻቶች እና እነዚህ የፈጠሯቸው የሴራ መንገዶች የታሰበላቸውን ግብ ሳይመቱ ባክነዋል።

የሕዝባችንን የዘመናት መሻት /ከትናንት የመሻገር ህልም ተጨባጭ ከማድረግ ይልቅ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንደሚባለው ያለውን አሳጥተውታል፤ የነበረውን አጥቶ በነበረው ነገር ተስፈኛ እንዲሆን፤ የማንነቱ መገለጫ ከነበሩ እሴቶቹ ወጥቶ፣ ከሚያወግዛቸው፣ ከሚጠየፋቸው እና ከሚረግማቸው ያልተገቡ ተግባራት ጋር እንዲለማመድ አድርገውታል።

ይህ ትውልድ ግን ከዚህ ሁሉ የትናንት ትውልዶች ስህተት ተምሮ፤ትናንቶችን በመድገም ከሚፈጠር የከፋ የታሪክ ስህተት እራሱን መታደግ በሚችልበት ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ውስጥ ነው፤ የሚያስፈልገው ለዚህ የሚሆን ስክነት፤ ከስክነት የሚመነጭ ሃላፊነት እና ከራስ እውነተኛ ማንነት ጋር የመታረቅ ቁርጠኝነት ነው።

ስክነት፤ ከስክነት የሚመነጭ ኃላፊነት እና ከራስ እውነተኛ ማንነት ጋር የመታረቅ ቁርጠኝነት በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶች መሻት የሆነውን ትናንትን ተሻግሮ ብሩህ ወደሆኑ ነገዎች የሚደረግ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ጅማሬ ነው። ይህን ማድረግ ደግሞ የመሻታችን የፍጻሜ ጅማሬ ነው።

የዛሬው የለውጥ ጉዟችንም የዚህ ታሪካዊ እውነት አካል ነው፤ ከትናንቶች ጋር አብረን ከኖርንባቸው ረጅም ዘመናት አኳያ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ የማለፍ አስገዳጅ ሁኔታዎች ቢኖሩም እነዚህ ፈተናዎች ግን በትውልድ ውስጥ ካለ የመሻገር መነቃቃት የሚበልጡ ባለመሆናቸው ፈተናዎቹን የመሻገር ተስፋችን በእጅ በደጃችን ነው።


አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በመሻገር ጥሪት ወደ አዲስ ብርሃን

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሸክታብ)

ወርሃ ነሐሴ ከነነጎድጓዱ እልቀ፣ ወርሃ ጳጉሜ ከተስፋው ጋር ደግሞ ከተፍ አለ። በአስራ ሶስት የወራት ጸጋ ዘመኗን ያሰላችው ሀገራችን ኢትዮጵያ የልዩ የመሆንን ስም ካተረፈችባቸው አጋጣሚዎች መሀል አንዱ ይሄ አጋጣሚ ነው። አሮጌውን ከነግሳንግሱ ሸኝተን በተስፋና በበጎ መሻት አዲሱን ዓመት የምንቀበልበት በተለይም ደግሞ በብዙ መንገጫገጭ ውስጥ ላለፈችው ሀገራችን በተግባቦት ብርሃንን መውለድ ከምኞቶቿ መሃል ነው።

በየዓመቱ ጳጉሜን ተንተርሰን በአሮጌው ዓመት ማብቂያና በአዲስ ዓመት አፋፍ ላይ ቆመን የምንመኘው ብዙ መልካም ምኞት አለን። ዘንድሮው እንዳለፈው ጊዜ ‹የመሻገር ጥሪቶች፣ የአዲስ ብርሃን ወረቶች› በሚል መነሻ ሃሳብ ወደ አዲሱ ዓመት የሚያንደረድረንን በኩረ መሻት ጀምረናል። በዚህ መነሻ ሃሳብ ስር ‹ጥሪት› ማለት ሀብት፣ ውርስ፣ ትውፊት ማለት ነው። ሁሉም ትርጓሜ ሀገርና ሕዝብ ላይ የሚያርፉ ብዙሃነትን ገላጭ ጽንሰ ሃሳቦች ናቸው። በጋራ ውርስ፣ በጋራ ሃሳብ፣ በጋራ ትውፊት የአዲስ ብርሃን ወረቶችን እንፍጠር የሚል ጠቅለል ያለ ትርጓሜ ያለው ይሆናል።

መሻገር ማለፍ ነው። ወደአዲስ ብርሃን፣ ወደተስፋ፣ ወደጋራ ትርክት መተላለፍ ነው። ከፉክክር ወደምክክር፣ ከችግር ፈጣሪነት ወደመፍትሄ አመንጪነት ሽግግር ነው። የመሻገር ጥሪቶች ሰላምን ማዕከል ያደረጉ፣ በሀገርና ሕዝብ ሉዓላዊነት የማይደራደሩ እሴቶች ናቸው።

> **መ**ሻገር ማለፍ ነው። ወደአዲስ ብርሃን፣ ወደተስፋ፣ ወደጋራ ትርክት መተላለፍ ነው። ከፉክክር ወደምክክር፣ ከችግር ፈጣሪነት ወደመፍትሄ አመንጪነት ሽግግር ነው። የመሻገር ጥሪቶች ሰላምን ማዕከል ያደረጉ፣ በሀገርና ሕዝብ ሉዓላዊነት የማይደራደሩ እሴቶች ናቸው

እነርሱም እንደእርቅና ተግባቦት፣ እንደአንድነትና ህብረብሄራዊነት ያለ ትርጓሜ ያላቸው ናቸው። አሁን ባለው የፖለቲካ መልክና ሀገራዊ ውኸንብር የመሻገር ጥሪቶች ዋጋቸው በምንም የማይተካ ነው። ጳጉሜን በዚህ ልዕለ ሃሳብ ሰይመን ወደብርሃናማ ነገ የምናደርገው ጉዞ እንዳለፈው ጊዜ በወሬ ብቻ እንዳይቀሩ በማስተዋል ቀኑን ማሰብ ተገቢ ነው።

ባለፉት ዓመታቶች እንዲህ ባሉ የአዲስ ዓመት አፋፎች ላይ ተስፋን ጫሪ ንግግሮችና ጽሁፎችን አሰራጭተናል። ምኞታችን ከሃሳብ አልፎ ወደ ተግባር ካልተንጸባረቀ መሪ ሃሳብ ብቻውን የተሃድሶ መንገድ አይሰጠንም። ተስፋንና ሰላምን ምኞቱ ላደረገ ማህበረሰብ መሻገር ብዙ ትርጓሜ አለው።

በፖለቲካና በሰጣ ገባ ያልተሻገርናቸው በርካታ ችግሮች አሉብን። በጦርነትና በመርዘኛ ትርክት አነካክሰው ሊጥሉን የተጠመዱ የክፋት ወጥመዶች ስር ነን። ስለሆነም ከጋራ እምነት የፈለቀ አግባቢና ለአዲስ ወረት የሚያበቃ የመሻገር ጥሪት ግድ ይለናል።

ጭንጋፍ ሃሳብ ጭንጋፍ ፖለቲካና ሀገር ነው የሚፈጥረው። የጨነገፍነውና እየጨነገፍን ያለነው ለመሻገር የሚያበቃ ከእኔነት ወደብዙሃነት የተላለፈ ኢትዮጵያዊነትን ያገነነ ሃሳብና እምነት ስላላዳበርን ነው። ጽንሶቻችን ሀገር ወልደውና ትውልድ አቅፈው አያውቁም። ሃሳቦቻችን ባልተገባ አስተሳሰብ ተሞርደው እሾህና አሜኬላ እያበቀሉ ብዙ በዋጋ አስከፍለውናል። ‹የመሻገር ጥሪቶች የአዲስ ብርሃን ወረቶች› የሚለው የአዲስ ዓመት መግቢያ ሀቲት ከዚህ አይነቱ ልምምድ ወጥተን በከበረ እሴትና በጋራ ሥርዓት ተከባብረን የሚከባበር ትውልድ እንድንፈጥር በማሰብ ነው።

የመሻገር ጥሪቶች አዲስ ተስፋን፣ አዲስ ብርሃንን የሚወልዱ ክበድ አስተሳሰቦች ናቸው። በሃሳቦቻችን ሀገራችንን የምንወልድበት፣ ህልሞቻችንን የምንታቀፍበት ወሳኝ ጊዜ ላይ ነን። ለትውልድ በሚተርፍ ተሻጋሪና አሻጋሪ ጥሪቶች ተነጋግረን በመግባባት መጪውን ጊዜ የሉዓላዊነታችን እና የእድገታችን ዋስትና ማድረግ እንችላለን።

የመሻገር ጥሪቶችን ሰውነትን የለወሱ አሻጋሪና ተሻጋሪ በሚል እንክፈላቸው እና እንመልከታቸው ..አሻጋሪ ስንል የሸር ትርክቶችን ሽረው ከትናንት ወደ አዲስ ዛሬ የሚመልሱ የኢትዮጵያዊነት ቀለም የፈሰሰባቸው ሲሆኑ ተሻጋሪ ስል ደግሞ እኛ ላይ ሳይቆሙ ወደነገ ተላልፈው ትውልዱን ከክፉ የአስተሳሰብ ደዌ ነጻ የሚያወጡ ብለን እንያቸው። አንድ ትውልድ ላይ ያልቆሙ አቃፊና አስታራቂ ጥሪቶች የወሳኝ ምዕራፍ መታጠፊያዎች ናቸው። ይሄን ወሳኝ መታጠፊያ የሚፈጥሩት ደግሞ ወደ አዲስ የብርሃን ወረቶች የሚያሸጋግሩ የመሻገር ጥሪቶች ናቸው።

አዲሱን ዓመት በተመሳሳይ መንገድ እንዳንቀበለው የሚያደርጉ ሰላምና አንድነትን መሠረት ያደረጉ በርካታ የሕዝብና የትውልድ ጥያቄዎች አሉ። ሰላም እንደዋነኛ ጥያቄ ሆኖ የሚነሳ ጉዳይ መሆኑ ሀቅ ቢሆንም የሰላም አማራጮችን አለመጠቀማችን እንዲሁ አብሮ የሚነሳ እንከናችንም ነው። አሁን ላለንበት ለየትኛውም አጀንዳ ወሳኝ ተዋናዮች እኛ ነን። ከዘመን ጋር በዘመነ ሃሳብና አመለካከት ወደፊት ለማቅናት ካልተሰናዳን በድሮና በነበር አሉባልታ ነጻ መውጣት አንችልም።

በተፈጥሮ ሂደት ዘመን ይመጣል ይሄዳል። አዲስ ዓመት ትርጉም የሚሰጠው በተቀየረ ልብና በተለወጠ አመለካከት ስንቀበለው ነው። የመሻገር ጥሪቶች አዲሱን ዓመት በአዲስ አእምሮና ልብ እንድንቀበለው፣ ስለሀገርና ሕዝብ ተቆርቋሪነት የሚሰማው ማንነት እንዲኖረን መሠረት የሚጥል ነው። ከነባርና ጠባብ ጠብ ወለድ ልምምድ ወጥተን ወደአዲስና ተራማጅ ሥርዓት የምናቀናበት እንዲሁም ከንቅቅፍ ወደትቅቅፍ ፖለቲካ የምናመራበት የአዲስ ዓመት አዲስ ገጸበረከታችን ነው።

በእውነት እና በጸና ልብ መሻገር የምንፈልጋቸው ብዙ ነገሮች አሉ። በአዲስ ዓመት አፋፍ ላይ ስለመሻገር ስናወራ ጳጉሜን በተለያዩ አንቂና አብቂ ሃሳቦች የመቀበል ልምድ ኖሮን ሳይሆን የእውነት መሻገር ስለሚያስፈልገን ነው። እዛም እዚም በተወለዱ መከራዎች መሀል ነን። ጦርነት አላባራም። ሰላም ቅንጦት ሆኖብናል። ለተነጋግሮ መግባባት አሻፈረኝ እያልን ነው እናስ መሻገር አያስፈልገንም?

የአዲስ ብርሃን ክስተቶች በሰማያችን ላይ የለም። ጦርነትና ጸብ እንደአልቦ በላያችን ላይ ፋፍተዋል። ደመና ባረገዘ የሞት ቀለያት እስከመች እንዳምናለን? እያረገዝን ስናስወርድና እየተመኘን ስንከሽፍ ብዙ ዘመናት ጠብተዋል። ተስፋችን ምኞታችንን ካልወለደ፣ ምኞታችን ፍቅርና የእርስ በርስ ትስስርን ካልሰጠን ዋስትናችን በምንም አይረጋገጥም። የመሻገር ጥሪቶች ወደሕይወታችን፣ ወደፖለቲካው፣ ወደትውልዱ፣ ወደማህበረሰቡ ወርደው አዲስ ዘርን እንዲያዘሩ የአዲስ ዓመት ተስፋችን ነው።

# ነፃ ሃሳብ

## አኩሪና ዕምርታዊ ድሉቻችንን እናሻግር !

**አዶኒስ (ከሲኤምሲ)**

“እዮሀ አበባዬ መስከረም ጠባዬ ፤ መስከረም ሲጠባ አደይ ሲፈነዳ እንኳን ሰው ዘመዱን ይጠይቃል ባዳ” ብለን ጆሮ ገብ በሆነው የልጆች ዝማሬ ነው አሮጌውን ዓመት ሸኝተን አዲሱን ዓመት የምንቀበለው። አዲሱ ዓመት አዲስ የሚሆነው በለመድነው እሳቤ በለመድነው መልኩ ስንቀበለው አይደለም። እንደመስከረም አበባ ሁሉ ዘመኑ የፈካና ያማረ፣ የሚያስደስት፣ የብዙዎችን ዓይን የሚስብ፤ መልካም ዜና የምንሰማበትና የምናወራበት ሆኖ እንዲያልፍ በመመኘት ፤ ምኞታችንን ለማሳካት አዳዲስ እቅዶችን በማቀድና ለመፈጸም ቃል በመግባት ነው።

መስከረም ሲጠባ እንኳን ሰው ዘመዱን ይጠይቃል ባዕዳ የሚባለው ዘመን ሲለወጥ የአስተሳሰብ ለውጥ አድርገን ሁሉንም እኩል የምናይበት ፣ የምንጠያየቅበት፣ ቂምና ቁርሾ ትተን በአንድነት ለአንድነት የምንተጋበት እንዲሆን የምንመኝበት ጊዜ እንዲሆንልን በመመኘት ጭምር ነው። ጎጂ ትርክቶችን ጥለን የሚጠቅሙንን የምናሻግርበት ዘመን እንዲሆን በማሰብ ጭምር ነው።

አዲስ ዓመት አዲስ ተስፋ የሚሰነቅበት፤ አዲስ ዕቅድ የሚተለምበት፤ እቅዱን ለማሳካት ቃል የሚገባበት እንደ በጎ ጅማሮ እና አዲስ ምዕራፍ የሚወሰድበት እንደመሆኑ መጠን መንግሥትም ሆነ ሕዝብ አዲሱን ዓመት ለመቀበል የሚዘጋጁት አዲስ ተስፋን በመሰነቅ፤ በሁሉም መስክ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ በቁርጠኝነት በመዘጋጀት ነው። የተቸገሩትን የምንረዳበት፣ የተጎዱትን የምንክስበት፣ መልካም የሆኑ እሳቤዎችን ሁሉ የምናሻግርበት ነው።

እንደ ግለሰብ ያለፉ መጥፎ ባህሪያትን፣ አስቸጋሪ የሚባሉ የሕይወት ውጣውረዶችን ለማቆም የሚወሰንበት አዳዲስ የሕይወት ምዕራፍ የሚጀመርበት በመሆኑ በአዲስ ዓመት ልዩ ልዩ ስንቆችን ሰንቆ መልካም የሆኑትን እርሾዎች ይዞ ወደፊት ለመራመድ መሠረት የሚጣለው በወርሀ መስከረም ነው።

እንደ ሀገርና መንግሥትም ባለፈው ዓመት የነበሩ ጠንካራ ጎኖች ሰፍተውና ለምልመው የሚቀጥሉበት መጥፎ፣ አስቸጋሪና ፈታኝ የነበሩትን አራግፎ ድክመቶችን አርሞ መልካም እድሎችን አስፋፍቶና አጠናክሮ አዲስ ተስፋ የሚሰነቅበት ዘመን እንዲሆን በመመኘት ብቻ ሳይሆን አቅዶ በመሥራትና በማሰራት ነው። ጳጉሜም አሻጋሪ ድልድይ ናት ያለፈውን ዓመት ደህና ሰንብት ብላ ትሸኛለች አዲሱን ዓመት ደግሞ እንኳን በሰላም መጣህ ብላ ትቀበላለች። ጳጉሜን አንድ ቀንም በመንግሥት የመሻገር ቀን ተብሎ ሲሰይም መልካም የሆኑ አስተሳሰቦችን ማሸጋገርን ታሳቢ በማድረግ ነው።

ያሳለፍናቸው ስድስት የለውጥ ዓመታት በየዘርፉ አኩሪና ዕምርታዊ ድሎች በማስመዝገብ ሀገር ማስቀጠል የተቻለበት ጊዜ ነበር። በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በኢነርጂ፣ በቱሪዝም፣ በሸገር ፕሮጀክት፣ በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት፣ የአቅመ ደካሞችን የመኖሪያ ቤት በመገንባት፣ በተማሪዎች ምገባ፣ በታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ የእርማት ሥራ፣ በሥራ እድል ፈጠራ፣ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፣ በልማት ኮሪደር፣... አቅዶ በመፈጸም፣ ፈጽሞ ሪቫን በመቁረጥ ብዙ ሊነገርለት የሚገባ፤ ትምህርት የሚቀሰምበት እና ለቀጣይ ሀገራዊ ድሎች እንደወረት ሊወሰድ የሚችል በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል፤ እጅን አፍ ላይ የሚያስጭኑ አስደማሚ ውጤቶች ተገኝተዋል። ይሄንን መልካም ስኬት በቀጣዩ ዓመት አሻግረን የምናስቀጥለው ከሀገር አልፈን ዓለምን በማስደነቅ ጭምር ሊሆን ይገባል።

ባለፉት የለውጥ ዓመታት የማንሻገራቸው ይመስሉን የነበሩ ነገር ግን በተደረገው ሀገራዊ ርብርብ ትልቅ ድል የተቀናጀንባቸውን የግብርና ሥራዎቻችንን በዛሬ የመሻገር ቀን አንዱን ማሳያ ማስታወስ የግድ ይላል። ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያ በአትሌቲክስ ድል ከምንታወቅበት በተጨማሪ መገለጫችን የስንዴ ልመና እንደነበር የምንዘነጋው ታሪክ አይደለም። ዛሬም ከአእምሯችን የፋቅነው ሳይሆን ታሪካችንን ለመቀየር መሠረት መጣል የጀመርንበት ወቅት ላይ እንገኛለን። በግብርና ዘርፍ ከስንዴ ልመና ወጥተን የውስጥ ፍጆታችንን በመቻል ለመጀመሪያ ጊዜ ስንዴ ለውጭ ገበያ ወደ ማቅረብ የተሸጋገርንበትን የመጀመሪያው የታሪክ ምዕራፍ ነው።

እንደ ግለሰብ ያለፉ መጥፎ ባህሪያትን፣ አስቸጋሪ የሚባሉ የሕይወት ውጣውረዶችን ለማቆም የሚወሰንበት አዳዲስ የሕይወት ምዕራፍ የሚጀመርበት በመሆኑ በአዲስ ዓመት ልዩ ልዩ ስንቆችን ሰንቆ መልካም የሆኑትን እርሾዎች ይዞ ወደፊት ለመራመድ መሠረት የሚጣለው በወርሀ መስከረም ነው

ኢትዮጵያ ካሏት ዜጎች ከ80 ሚሊየን በላይ አርሶ አደር ቢሆንም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ግን ስንዴን ጨምሮ የምግብ ሰብሎችን በከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ ከውጭ ሀገር ታስመጣ ነበር። የምግብ ፍጆታ ምርቶችን ከውጪ ማስገባት ሀጢያት ባይሆንም ሀገሪቱ ካላት የውጪ ምንዛሬ አቅም አንጻር በኢኮኖሚው ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ከዚህም በተጨማሪ ከስንዴ ጋር ተያይዞ የነበረው ፖለቲካዊ ትርጉም የዜጎችን አንገት ቀና የሚያስደርግ ሳይሆን አንገት የሚያስደፋና እጅ የሚያስጠመዝዝ እንደነበር የምናስታውሰው ነው።

ይሁን እንጂ በቁጭትና በጥንካሬ ይሄንን ታሪክ ለመቀየር በ2011 ዓ.ም በ3ሺ 500 ሄክታር መሬት ላይ የተጀመረው የስንዴ የመኸር እርሻ አሁን በጋና መኸሩን ጨምሮ በተሰራው የግብርና ሪፎርም ፣ በኩታ ገጠም እርሻ ዛሬ ከሀገር ውስጥ የምግብ ፍላጎት አልፎ ለውጭ ገበያ እስከ ማቅረብ ተደርሷል። ይሄ ከምንም የተገኘ ሳይሆን በበሳል እስትራቴጂ ዕቅድ፣ በራሳችን መሬት፣ በራሳችን አርሶ አደርና ባለሀብት በቆራጥነት በተሰራ ሥራ በበሳል አዕምሮ በተመራ የአመራር ብቃት የተገኘ ውጤት ነው።

ዛሬ ከነበርንበት የስንዴ ገበያ እና የስንዴ ርዳታ ወጥተን ስንዴን ለውጭ ገበያ አቅራቢነት የተሸጋገርንበት በኩራት የምንናገረው ዓለም ጭምር የመሰከረው ነው። አሁንም በዚሁ እንቆማለን፣ በዚሁ ረክተናል ለማለት አይደለም ቀጣዩ ዓመት ከዚህ ባለፈ ቴክኖሎጂዎችን፣ አዳዲስ ስትራቴጂዎችን ተጠቅመን፣ በአንድነትና በጥንካሬ ለተሻለ ለውጥ የምንሰራበት ለዚህም ቃል የምንገባበት ወቅት ላይ ነን።

በኢንዱስትሪው መስክ ኮቪድ 19 ያሳደረውን መጥፎ ተጽዕኖ የሀገሪቱ አጠቃላይ የማምረት አቅምን የተፈታተነ እንደነበር የምናስታውሰው ነው። ያኔ የበርካታ ኢንዱስትሪዎች ሥራቸው የተቀዛቀዘበት፣ ገበያ ያልነበረበት፣ በርካታ ችግሮች የተስተናገዱበት ነበር። ይሄንን የኢኮኖሚ ስብራት ለመጠገን በተሰራው ሥራ በርካታ ኢንዱስትሪዎች ከቆሙበት ወደ ተሟላ ማምረት እና የተኪ ምርት ትግበራ ተሸጋግረዋል። ኢንዱስትሪዎቹ በተሻለ መልኩ በማገገማቸው ዛሬ ሠራተኞችን በመቅጠር ለብዙዎች የሥራ ዕድል ከፍተዋል። ዜጋው የሀገር ምርቶችን እንዲጠቀም ምቹ ሁኔታን ፈጥረዋል። በቀላሉ በሀገሪቱ የሚገኙ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ዩኒፎርም ለዚህ አንዱና ትንሹ ማሳያ ነው።

በ2003 ዓ.ም በወርሃ መጋቢት 24 የመሠረት ድንጋይ ተጥሎ በኢትዮጵያውያን ገንዘብ፣ ጉልበትና እውቀት የተጀመረው የኢትዮጵያውያን ኩራትና መለያ የሆነው ታላቁ የሕዳሴ ግድብ በታየበት ብልሹ አሰራርና የፕሮጀክቶች የመምራት አቅም ውስንነት ተንገራግጮ በመቆሙ ብዙዎች አዝነውና ተስፋ ቆርጠው ነበር። ይሁን እንጂ የብልጽግናው መንግሥት” እንደጀመርን እንጨርሰዋለን” የሚለውን መርህ ወደፊት በማምጣት ባደረገው ጥልቅና ሰፊ ግምገማ የችግሮችን ምንጭ ተረድቶና በፕሮጀክቱ ላይ የነበሩ ስህተቶች ታርመውና ተስተካክለው እንዲቀጥሉ በሰጠው ቆራጥ አመራር ለሊት ከቀን በተደረገ ክትትል ዛሬ የተደረሰበት ደረጃ ላይ መድረስ ተችሏል።

የመላው ኢትዮጵያውያን ዐሻራ ያረፈበት ታላቁ የኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ የኢትዮጵያን እድገት የማይመኙ የውጭ ሀገራት ሥራውን ለማደናቀፍ በተደጋጋሚ ጊዜ በተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት አጀንዳ ሆኖ እንዲቀርብ ያላሰለሰ ጥረት አድርገዋል። አብሮ የመልማትና የጋራ ተጠቃሚነትን መርህ ያነገበው መንግሥት ግን አንድም ጊዜ ከዓላማው ሸብረክ ሳይል የልማት አደናቃፊ የሆኑ ክሶችን በበሳል ባለሙያዎችና አመራሮች ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ማክሸፍ በመቻሉና ሥራውም ጥራቱን ጠብቆ በመሰራቱ አሁን አራት ተርባይኖች ተጠናቀው የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ደረጃ ላይ ደርሰዋል።

በሕዳሴ ግድብ ግንባታ ትልቁ ስኬት ነው። ቀሪው ሥራም ሀገርን የሚፈትን ሳይሆን በአንድ ዓመት ውስጥ የሚጠናቀቅ ሆኖ ዕቅድ ተይዞለታል። ጊዜ ተቆርጦለታል። ይሄ የሀገር ኩራት ለጠላት የውስጥ እግር እሳት ሆኖ ቀጥሏል። እያንዳንዱ ዕቅድ እያንዳንዱ ፕሮጀክት ሲሰራ በርካታ ተግዳሮቶች የማይታለፉ የሚመስሉ ግን የታለፉ ችግሮች አጋጥመዋል። በየአካባቢው የሚታዩ የሰላም መደፍረሶች በሥራው ላይ የፈጠሩት መሰናክል ሕይወትን ጭምር ያስገበሩ የሚያስገብሩ እንደነበሩ ማስታወስ የግድ ይላል።

በቱሪዝም ዘርፍ ኢትዮጵያ ያላት አቅምና ሀብት፣ ሰው ሠራሽና ተፈጥራዊ ጸጋዎች ዓለምን የሚያስደምም ዕድል ቢሆንም በልኩ ሳትጠቀምበት ቆይታለች። የጎረቤት ሀገራትን የቱሪዝም ሀብት እያዩ ከማድነቅ ይልቅ ተስፋ ያለው ሥራ አልተሰራም። አሁን ግን ይሄንን ታሪክ የሚቀይር ከመሀል አዲስ አበባ እስከ ክልሎች የሚደነቅ ለዓይነ ሳቢና አስደማሚ የቱሪዝም መዳረሻዎችን መገንባት ተችሏል። የአፍሪካዊያን መኩሪያ የሆነች የቱሪዝም መናኸሪያነት የተሸጋገርንበትን ዘመን ላይ ደርሰናል።

የአንድነት ፓርክ ፣ የወዳጅነት ፓርክ ፤ የእንጦጦ ፓርክ፣ የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች የወንጪ ዳንዲ፣ የጎርጎራ፣ የጨበራ ጩርጩራ፣ የዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም... የቱሪስትን ዓይን የሚስቡ ታይተው የማይጠገቡ ትልልቅ ፕሮጀክቶች ናቸው። በሰው ሠራሽ ሐይቆች የተከበበው የሀገራችን ቅንጡ ሪዞልቶች እነ ሃላላኬላ ተመርቀው በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን አስተናግደዋል። የገቢ ምንጭ መሆን ጀምረዋል። ይሄ ቁጭ ብሎ መናን ከሰማይ በመጠበቅ የተገኘ ውጤት አይደለም። ይሄ መሥራት እንደሚቻል ተሰርቶም ውጤቱ በተጨባጭ የታየበት የአመራር በተለይም የጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ የማቀድ፣ የመምራትና የመፈጸም አቅምን ልክ ያሳየ ነው።

ሁልጊዜም “ማቀድ ብቻ ሳይሆን ጨርሰን ሪቫን እንቆርጣለን” የሚሉበትን አንደበታቸውን በተጨባጭ ያስመሰከሩበት ሥራዎችና ፕሮጀክቶች ናቸው። ይሄ ትምህርት የቀሰምንበት፣ የእውቀት ሽግግር የተደረገበት፣ መሥራት መለወጥ እንደሚቻል የታየበት ነው። በቀጣይም ለተሻለ እቅድና ሥራ ለመሥራት መንግሥትና ሕዝብ የሚነሳሱበት አንዱና ትልቁ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ይሆናል።

ከዚሁ አመርቂ ስኬት ጎን ለጎንም በርካታና ውስብስብ ፈተናዎችን ባለፉት ዓመታት አጋጥመዋል። በተለይ ከሰላምና ጸጥታ ጋር ተያይዞ፣ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች፣ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ሁሉ ዓይናቸውን አፍጥጠው ጥርሳቸውን አግጥጠው መጥተው አልፈዋል። ለነገ የቤት ሥራ ሊሆኑ የሚገቡ ትምህርት የሚወሰድባቸውና የተወሰደባቸውም ነበሩ። ይሁን እንጂ ከሞላ ጎደል ሁሉንም መሻገር ተችሏል ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል፡፡

መጪው አዲስ ዓመት ደግሞ የነበሩ ድሎቻችንና ስኬቶችን ይበልጥ የምናሰፋበት፣ ተግዳሮቶቻችንን የምንቀንስበት ዓመት ሊሆን ይገባል። የተመኘነው ስኬትም በውጤታማነት ለማስቀጠል የትናንቱን መለስ ብለን መቃኘት ያስፈልጋል። ስህተቶቻችንን ማረም፣ ችግሮቻችንን በምክክር በመግባባት መፍታት፤ የሚጠቅሙንን ትርክቶቻችንን ወደፊት አስቀድመን የማይጠቅሙንን ጥለን የወደፊቷን ኢትዮጵያ ማየትና ማለም ይገባል። ልዩነታችንን ማጥበብ በፖለቲካው ዘርፍ ልንሰራቸው የሚገቡን የቤት ሥራዎች ናቸው።

ኢትዮጵያውያን ታሪካችንን የምናስቀጥለው በጦርነት ብቻ ያገኘናቸውን ድሎችን በማንሳትና በማወደስ ብቻ መሆን የለበትም። በየዘመኑ የተሰሩና የሚሰሩ የልማት አርበኛ ያደረጉንን ታሪኮቻችንን ጭምር ወደፊት በማምጣት ፤ እዛ ላይ ቆመን የነገዋን ሀገር በተሻለ መንገድ በማሰብና ለዛም አቅደን በማሳካት ነው። ለዚህ ደግሞ የዛሬው ስኬቶችና ድክመቶቻችንን ትምህርት አድርገን ልንወስድ ይገባል። የጎደለውን ሞልተን፣ ያነሰውን አብዝተን፣ የጠበበውን አስፋፍተን ሀገራችንን ወደ በለጸጉት ሀገራት ተርታ ማሰለፍ ይጠበቅብናል። በዛሬው የመሻገር ቀን መልካም መልካሙን ተሞክሮ እናሻግር መልዕክታችን ነው። ቸር እንሰንብት!

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ቆሻሻን ወደ ሀብት

**ክብረአብ በላቸው**

በዚህ ዘመን ቴክኖሎጂ ከትምህርት፣ ከጤና፣ ከግብርና እና ከሌሎች ዘርፎች አንፃር የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ላሉና በማደግ ላይ ለሚገኙ ሀገራት ደግሞ የቴክኖሎጂ ፋይዳ ከምንለው በላይ ትልቅ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች ላይ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የማደግ ዕድል እንዳላት ሀገር ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን ጥረት እያደረገች ትገኛለች። በሁሉም መስክ ማለትም የማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል፣ ዘመናዊ ትምህርት ተደራሽ ለማድረግ፤ ግብርናን ዘመናዊ በማድረግ በምግብ እራስን ለመቻል፣ ለጤና ብሎም ለወታደራዊ አገልግሎት፣ በአጠቃላይ በሁሉም ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን በቴክኖሎጂ መታገዝ የግድ ሆኗል።

በተለይ በምግብ እራስን ችሎ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የማገዝ ጉዳይ ከልማዳዊ አሠራር ሥርዓት ማላቀቅ መቻል እንዳለበት ብዙዎች ይስማማሉ። ሰፊ ለም መሬት፣ ከፍተኛ መጠን ያለው የገጸ ምድርና የከርሰ ምድር ውኃ፣ ተስማሚ የአየር ፀባዮች፣ እንዲሁም ከፍተኛ የሆነ ወጣት የሰው ኃይል ባለበት ሀገር ውስጥ በምግብ ዕጦት መቸገር መብቃት ያለበት ጉዳይ እንደሆነ ይታመናል።

ወጣት አዜብ የማነህ ትበላለች ውልደትና ዕድገቷ በመዲናችን አዲስ አበባ ከተማ ነው። ከመጀመሪያው እስከ ሁለተኛ ደረጃ ያለውን ትምህርቷን በአደገችበት አካባቢ በሚገኙ የተለያዩ ትምህርት ቤቶች የተከታተለችው አዜብ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቷን ለመከታተል ወደ ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በማቅናት በተፈጥሮ ሀብት አስተዳደር በመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቃለች።

ወጣት አዜብ ከከፍተኛ ትምህርት ቆይታዋ በኋላ ወደ ሥራው ዓለም ስትሰማራ የመጀመሪያ ሥራዋን የጀመረችው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ኤጀንሲ የፅዳት አስተዳደር ኃላፊ በመሆን ነበር። በተለያዩ ምክንያቶች በሥራው መቀጠል ባትችልም ይህ ሥራዋ ለዛሬ የፈጠራ ግኝቷ መነሻ ስለመሆኑ ትናገራለች።

ከደረቅ ቆሻሻ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ማምራት የቻለችው ወጣት አዜብ ለዚህ የፈጠራ ሥራዋ መነሻ ስለሆናት ነገር ስትናገር፤ ‹‹በልጅነታችን ለምግብነት የሚውሉ የእህል ዓይነቶችን የምንገዝበት ዋጋ በጣም ዝቅተኛ ነበር። ለአብነት ጤፍ ከሀምሳ እስከ መቶ ብር ይገዛ ነበር’’ የምትለው አዜብ፤ በአሁኑ ወቅት ግን የእህል ዋጋ በየጊዜው እየጨመረ መጥቶ አነስተኛ ገቢ ያለው የኅብረተሰብ ክፍል ዋጋውን መቋቋም የማይችልበት ደረጃ ደርሷል። ይህ እንደ አንድ ዜጋ በእጅጉ ያሳስበኛል ትላለች።

የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ሁልጊዜ ዘርተው ካጨዱ በኋላ ለቀጣይ ዓመት ለዘር የሚሆናቸው እህል ያስቀምጣሉ የምትለው አዜብ፤ ታዲያ የምርታማነት ችግሩ ከምን የመነጨ ነው? በሚል በጉዳዩ ዙሪያ የተለያዩ መረጃዎችን ለማየት ጥረት በምታደርግበት ወቅት የምርታማነት ችግሩ መነሻ በሀገሪቱ በግብርና ሥራ የተሰማሩ ግለሰቦች በተደጋጋሚ የኬሚካል ማዳበሪያ በመጠቀማቸው መሬቱ በከፍተኛ ደረጃ በአሲዳማነት በመጠቃቱ የተፈጠረ ችግር ስለመሆኑ እንደተረዳች ትናገራለች።

አርሶ አደሮች በአሁኑ ወቅት በአንድ ሄክታር መሬት 80ኪሎ የኬሚካል ማዳበሪያ ቢጠቀሙ በሚቀጥለው ዓመት በተመሳሳይ መሬት ላይ ቢያንስ አንድ ሶስተኛ ተጨማሪ ማዳበሪያ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል የምትለው አዜብ፤ ይህ ከልሆነ መሬቱ ምርት መስጠት አይችልም። ይህ እንደ ሀገር እየተስፋፋ ለመጣው የአፈር አሲዳማነት የራሱን ሚና ተጫውቷል ትላለች።

በዚህ መነሻ አርሶ አደሩ እራሱ በስጋት ላይ ነው ያለው የምትለው የፈጠራ ባለሙያዋ አዜብ፤ ይህ እንዳለ ሆኖ ከፍተኛ የኬሚካል ማዳበሪያ ዕጥረት አለ፤ አርሶ አደሩ ክረምት በመጣ ቁጥር የኬሚካል ማዳበሪያውን በወቅቱ ካላገኘ መሬቱ ፆሙን አደረ ማለት ነው። ይህ ደግሞ እንደ ሀገር የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ላይ ጥላ ያጠላ በመሆኑ ይህንን ለመቅረፍ በማሰብ ነው ወደ ፈጠራ ሥራው የገባሁት ትላለች።

በአሁኑ ወቅት በብዛት አገልግሎት ላይ የሚውለው የኬሚካል ማዳበሪያ ከአየር ንብረት፣ ከዋጋ፣ ከአርሶ



አደር ተደራሽነት አንፃር ያለው ችግር የሚታይና ጉልህ ነው የምትለው ወጣት አዜብ፤ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ገበሬው መግዛት በሚችለው ተመጣጣኝ ዋጋ የተሻለ ምርት መስጠት የሚችል ማዳበሪያ እሷና ጓደኞቿ ይዘው እንደመጡ ትናገራለች።

‹‹የተፈጥሮ ማዳበሪያን ለማምራት የምንጠቀመው ከቤት ውስጥ የሚወጡ ተረፈ ምርቶችን ነው›› የምትለው አዜብ፤ ‹‹የሰው ልጅ እስካለ ድረስ ተጠቅሞ የሚያስወግዳቸው ተረፈ ምርቶች ይኖራሉ፤ ይሄንን በአግባቡ ሰብስበን ፕሮሰስ አድርገን ስናወጣ መንግሥት ለማዳበሪያ ግዢ በየዓመቱ የሚያወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከማዳን ባለፈ ዜጎች ጤናማ ምግብ መመገብ እንዲችሉ ማድረግ እንደሚቻል›› ትናገራለች።

በኢትዮጵያ የአፈር አሲዳማነት በየዓመቱ 2 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር የሚገመት የሀብት ብክነት እያደረሰ እንደሚገኝ የምትናገረው ወጣት አዜብ፤ በየዓመቱ ከአንድ ሚሊየን ኩንታል በላይ ማዳበሪያ መስጠት ያለበትን ጥቅም ሳይሰጥ በአፈር አሲዳማነት ምክንያት ይባክናል። ይህ እንደ ሀገር ጉዳቱ ከፍተኛ ነው ትላለች።

እንደ ወጣት አዜብ ገለፃ፤ በኢትዮጵያ እየታረሰ ካለው 16 ሚሊየን ሄክታር መሬት መካከል 6.5 ሄክታር መሬት በአሲዳማነት የተጠቃ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ደግሞ 3.7 ሚሊየን ሄክታር የሚሆነው በጠንካራ አሲዳማነት የተጠቃ ነው። ይህም ጥቅም ላይ የዋለውን የእርሻ መሬት 40 በመቶ ድርሻ የሚሸፍን ነው ትላለች።

የተፈጥሮ ማዳበሪያ በፈሳሽ መልክ ብሎም የተለያዩ ተረፈ ምርቶችን በኮንቴነር በማድረግና ለ61 ቀናት በማብላለት እንዲደርቅ በማድረግ ኮምፖስት የሚያመርቱ አካላት አሉ የምትለው አዜብ፤ “እኛ የምናመርተውን ማዳበሪያ ልዩ የሚያደርገው ብዙ ነገሮች አሉት። ለአብነት በኮንቴነር 61 ቀናት ቆይቶ የሚወጣው ኮምፖስት እንደ ሀገር ችግርን ሊፈታ ስለማይችል በጥቂት ጊዜ በብዛት ማምራት መቻላችን ነው” ትላለች።

በከተማዋ በተለያዩ አካባቢዎች የተዘጋጁ የቆሻሻ መጣያ ሥፍራዎች በመሄድ የሚሰበሰቡ የቆሻሻ ዓይነቶች በተለያየ ዓይነት የሚለዩ የሚያደርቁና የሚያሞቁ ማሽኖች አሉ የምትለው አዜብ፤ እነዚህ ማሽኖች የተፈጥሮ ማዳበሪያው በብዛትና በጥራት ማምረት እንዲቻል እንደሚያደርጉ ትናገራለች።

የማዳበሪያ ምርቱን በአንድ ኪሎ፣ በሁለት ኪሎ፣ በአምስት ኪሎ፣ በአስር ኪሎ፣ በሃያ አምስት ኪሎ፣ በሃምሳና በመቶ ኪሎ በማዘጋጀት ለገበያ የማቅረብ ውጥን እንዳላት የምትናገረው አዜብ፤ በዚህ መልኩ ለገበያ እንዲቀርብ የታሰበው በግብርና ሥራ የተሰማራ ማንኛውም ሰው የሚፈልገውን የማዳበሪያ መጠን ገዝቶ መጠቀም እንዲችል መሆኑን ትናገራለች።

የኢትዮጵያ መንግሥት ለ2017/18 የምርት ዘመን 20 ሚሊየን ኩንታል በላይ የኬሚካል ማዳበሪያ ለመግዛት

> **መንግሥት በራሱ የግድ ምርት መመረት ስላለበት በማሰብ የኬሚካል ማዳበሪያ በከፍተኛ ወጪ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባል። ሆኖም የማዳበሪያ ምርቱ በዜጎች ጤና ላይ በረዥም ጊዜ ሂደት የሚፈጥረው ችግር ትኩረት የተሰጠው አይደለም**

እቅድ የነበረው ቢሆንም የቀረበለት 15 ሚሊየን ኩንታል ነው የምትለው አዜብ፤ ለዚህ ግዥ 15.5 ቢሊዮን ብር ወይም ከአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ወጪ ይደረጋል። ይህ እንደ ሀገር ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጫና የሚያሳድር ስለመሆኑ ታስረዳለች።

“እኛ የምናመርተውን የተፈጥሮ ማዳበሪያ አንድ ኩንታል በ885 ብር እንሸጣለን” የምትለው አዜብ፤ የኬሚካል ማዳበሪያ በመንግሥት ድጎማ ቀርቦ 2800 ብር ነው የሚሸጠው ከዚህ አኳያ ከፍተኛ የዋጋ ልዩነት አለው። ከዋጋው ተመጣጣኝነት ባለፈ የመሬቱን ጤናማነት ከመጠበቅ አንፃር የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው” ትላለች።

የኬሚካል ማዳበሪያ የእርሻ ማሳ ላይ አምና ከተጠቀምነው ሩብ ያህል ተጨማሪ ማዳበሪያ መጠቀም ያስፈልጋል የምትለው አዜብ፤ የተፈጥሮ ማዳበሪያውን ስንጠቀም ግን አንድ ጊዜ ከተጠቀምን ከሶስት እስከ አምስት ዓመት ያለ ተጨማሪ ማዳበሪያ ምርት መስጠት እንደሚችል ትናገራለች።

ሥራው ሰፊ እንደመሆኑ በመላው ሀገሪቱ ለማስፋፋት እቅድ አለኝ የምትለው አዜብ፤ ይህንን ህልም እውን ለማድረግ የተለያዩ ስልጠናዎችን እየወሰደች ስለመሆኑ ተናግራ፤ የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት ከቻለች ቴክኖሎጂውን በሀገር አቀፍ ደረጃ በማዳረስ ለግብርና ሴክተሩ ምርታማነት የራሷን ሚና ለመወጣት እንደምትፈልግ ትገልጻለች።

‹‹የሰው ልጅ መኖር ካለበት መብላት አለበት›› የምትለው አዜብ፤ በኢትዮጵያ በአብዛኛው የሚያጋጥሙ የበሽታ ዓይነቶች ከአመጋገብ ጋር የተያያዘ መሆኑን ትናገራለች። ኢትዮጵያ የኬሚካል ማዳበሪያን ተጠቅማ ስለማምርት አንዳንድ የውጭ ሀገር ዜጎች የኢትዮጵያን እህል አይጠቀሙም። ይሄ ማዳበሪያ በራሱ በዜጎች ጤና ላይ እያሳደረ ያለው ጫና በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ስለዚህ ወደ ተፈጥሮ መመለስ የውዴታ ግዴታ መሆን አለበት ትላለች።

‹‹መንግሥት በራሱ የግድ ምርት መመረት ስላለበት በማሰብ የኬሚካል ማዳበሪያ በከፍተኛ ወጪ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባል። ሆኖም የማዳበሪያ ምርቱ በዜጎች ጤና ላይ በረዥም ጊዜ ሂደት የሚፈጥረው ችግር ትኩረት የተሰጠው አይደለም የምትለው›› አዜብ፤ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ምርት ላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ትናገራለች።

የተፈጥሮ ማዳበሪያ የማምረት ሥራው በጥናትና ፋይናንስ ቢደገፍ ለትውልድ የሚተርፍ ሥራ መሥራት የሚቻልበት መስክ ስለመሆኑ የምትናገረው አዜብ፤ የመንግሥት ድጋፍ ባለው መልኩ ከተሰራ የኬሚካል ማዳበሪያውን ሙሉ በሙሉ ከገበያ በማስወጣት የገበሬውን የማዳበሪያ ፍላጐት ከማሟላት ባሻገር ጤናማ ምርት በማምረት የአመጋገብ ሥርዓታችንም ጤናማ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል ትላለች።

ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ትብብር እና አብሮ የመሥራት ፍቃደኝነትን በተመለከተ ወጣት አዜብ ስትናገር፤ ‹‹ተቋማት አብሮ የመሥራት ፍላጐት ቢኖርም መሟላት በሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ዙርያ ለሁሉም የሥራ ዓይነት ተመሳሳይ መመዘኛ ስለሚኖር ረዥም የቢሮክራሲ ሂደት ማለፍ ይጠይቃል፤ ይህ ደግሞ ተስፋ ያስቆርጣል። ስለዚህ የቴክኖሎጂ ሃሳብ ላላቸው የፈጠራ ባለሙያዎች አመቺ አሰራር ቢኖር የበለጠ ውጤታማ መሆን ይቻል ነበር›› ትላለች።

የብድር አቅርቦትን በተመለከተ እንደ ስታርት አፕ ሃሳብ ይዘን ነው የምንነሳው የምትለው አዜብ፤ ያንን ሃሳብ አይቶ ወይም የአዕምሮ ንብረት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት አይቶ ብድር የሚሰጥ ባንክ ቢኖር በሂደት ሥራው እየተሰራ ብድሩን መመለስ እንደሚቻል ተናግራ፤ ነገር ግን ይህ አሰራር አለመኖሩ እንደ ቴክኖሎጂ ኩባንያ በፈለግነው ልክ ወደፊት መራመድ እንዳንችል እያደረገ ነው ትላለች።

የመሥሪያ ቦታ ችግር ሥራዬን በፈለኩት መጠን መሥራት እንዳልችል አድርጎኛል የምትለው አዜብ፤ የፈጠራ ሃሳቡ ጠቃሚ ነው ወይስ አይደለም? ተግባራዊ መሆን ይችላል አይችልም? ለብዙ ሰው የሥራ ዕድል ይፈጥራል አይፈጥርም? የሚለው እንደ ሀገር በአግባቡ ታይቶ፤ የመሥሪያ ቦታ ችግሩ ቢፈታ በከፍተኛ ደረጃ ውጤታማ መሆን እንድንችል ያግዘናል ትላለች።

“በ2017 ዓ.ም እራሴን አጠናክሬ የመንግሥት ድጋፍ ተጨምሮበት ቴክኖሎጂውን ወደ ተለያዩ ክልሎች በማስፋትና ወጣቶችን በማሰልጠን ምርቱን በስፋት የማምረት እቅድ አለኝ” የምትለው አዜብ፤ በረዥም ጊዜ ሂደት ደግሞ የተፈጥሮ ማዳበሪያው ደረጃውን ጠብቆ በማዘጋጀት ወደ ውጭ የመላክ ሃሳብ እንዳላት ተናግራለች።

# የምድር በረከት

# ኢትዮጵያን ወደፊት ለማሻገር ተስፋ የተጣለበት የማዕድን ዘርፍ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኢትዮጵያ ተፈጥሮ የለገሰቻት የማዕድን ሀብት ከፍተኛ ክምችት ያላት ሀገር ብትሆንም ይህ ሀብቷ በተለያዩ ምክንያቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል አልተደረገም። ጥቅም ላይ አለመዋሉ ብቻ ሳይሆን በቅጡ እንዳልተጠናም መረጃዎች ያመላክታሉ። በመሆኑም ቀደም ባሉት ጊዜያት የማዕድን ዘርፉ ትኩረት ተነፍጎት በመቆየቱ የተነሳ እዚህ ግባ የሚባል ሥራ በዘርፍ አልተሰራም። በመሆኑም ሀገሪቷ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም ሳታገኝ ቆይታለች።

ይሁን እንጂ የማዕድኑ ዘርፍ ትኩረት ተሰጥቶት ከተሰራበት ገቢ በማመንጨትና የሥራ እድል በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ከመሆኑም ባሻገር የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት መሆን እንደሚችል ይታመናል። ታዲያ ሀብቱን በአግባብ አውቆና አልምቶ ጥቅም ላይ እንዲውል ከተደረገ አንዱ የኢኮኖሚ መሠረት ሆኖ ሀገር ከድህነት አረንቋ እንድትወጣ የሚያደርግና ወደፊት የሚያሻግር ነው።

ይህን ገና ያልተነካና ብዙም ያልተሰራበትን ሀብት በማልማት ሀገር ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ ብዙ ሥራዎች መሥራትን ይጠይቃል። በተለይ ኢትዮጵያ ያላትን ከፍተኛ የማዕድን ሀብት ክምችት በደንብ አጥንቶ፣ አውቆና ለይቶ ማልማት ከተቻለ የማዕድን ውጤቶችን ኤክስፖርት አድርጋ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ያስችላታል። ማዕድናቱን ወደ ውጭ በመላክ ከምታገኘው የውጭ የምንዛሪ ይልቅ ቅድሚያ ተሰጥቶት ከተሰራበት ከውጭ የምታስመጣውን የማዕድን ውጤቶችን በሀገር ውስጥ በማምረትና መጠቀም፣ ምርቱን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ይበልጥ ተጠቃሚ ልትሆን ትችላለች። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህም መንግሥት ለማዕድን ዘርፉ ትኩረት በመስጠቱ ከአምስቱ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች አንዱ አድርጎ በመወሰድ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ።

በዕለቱ ዝግጅታችንም የማዕድን ዘርፉ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ስለሚኖረው አበርክቶ ስናነሳ የዕለቱን የጳጉሜን 2 ቀን 2016 ዓ.ም መልዕክት ታሳቢ በማድረግ ነው። የጳጉሜን ቀናት በተለያዩ ስያሜዎች የተሰየሙ ሲሆን፤ ዛሬ ጳጉሜን 1 ቀን 2016 ዓ.ም የመሻገር ቀን "የመሻገር ጥሪቶች፤ የአዲስ ብርሃን ወረቶች " በሚል መሪ ሃሳብ ነው።

ኢትዮጵያ የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት ከምታደርጋቸው ዘርፈ ብዙ ጥረቶች መካከል ቁልፍ ሚና የሚጫወተው የማዕድን ዘርፍ እንደሆነ ይታመናል። ሀገሪቷ የማዕድን ሀብቷ ጥቅም ላይ ውሎ ሀገሪቷ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ ከማድረግ ባሻገር የኢኮኖሚ መሠረት ሆኖ ወደፊት መሻገሪያ ድልድይ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ ሀገሪቷ ያላትን አቅምና አሁን ላይ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችን አስመልክቶ የሚከተለውን አሰናድተናል።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት ከሆነ ኢትዮጵያ ከዓለም የማዕድን ክምችት አኳያ ስትመዘን በርካታ የማዕድናት ዓይነቶች ስላሉት ስማቸው በአንደኝነት ከሚጠቀሱት መካከል ትገኛለች። ይህን ከፍተኛ የማዕድን ክምችቷን በዓይነት ስንመለከትም ወርቅ፣ የከበሩና ጌጣጌጥ፣ ፖታሽ፣ ሊትየም፣ ኮፐር፣ ማንጋኒዝ፣ ክሮማይት፣ የፎስፌት፣ ኒኬል፣ ጨው፣ ለኢንዱስትሪ (የታንታለም፣ ብረት እና ብረት ነክ ማዕድናት እና ሌሎች)፣ ለኮንስትራክሽን (የድንጋይ ከሰል፣ አሸዋና ሌሎች)) ግብዓት የሚውሉ ማዕድናት፣ የኢነርጂ፣ የጂኦተርማል ማዕድናት፣ በአሁኑ ወቅት በዓለም እጅግ ተፈላጊ የሆኑ እና የሌሎች ማዕድናት ዓይነቶች ይገኙባታል። በተለይም በዓለም ላይ እጅጉን ተፈላጊ የሆኑ አረንጓዴ ቴክኖሎጂን ለማምረት ከፍተኛ አቅም ያላቸው ማዕድናት መገኛ መሆኗን መረጃዎች ያመላክታሉ።

ከማዕድን ሚኒስቴር የተገኙ መረጃዎችም ይህንን የሚያጠናክሩ ናቸው። ሀገሪቱ ያሏት የማዕድን ሀብት ዓይነትም ሆነ ክምችት መጠን በትክክል ስለማይታወቅ ይህን ለማወቅ በየጊዜው ጥናቶች ይካሄዳሉ። ይሁን እንጂ እስካሁን በተደረገው የዳሰሳ ጥናት የክምችት መጠናቸው የታወቀ ማዕድናት መኖራቸው ይጠቁማሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ወርቅ ሲሆን በሀገሪቱ ከ517 ቶን በላይ የወርቅ ክምችት መኖሩ ተረጋግጧል። በከበሩት ማዕድናት ዘርፍ ከ40 ያላነሱ ድንቅ እና ውድ የሆነ ዋጋ ያላቸው ማዕድናት አላት። ሀገሪቱ ከዓለም ግዙፉ ያልለማ የፖታሽ ክምችት ካላቸው ሀገራት አንዷ ናት። በደናክል ተፋሰስ ውስጥ ከ26 ቢሊዮን ቶን በላይ የፖታሽ ሀብት የሚገኝ ሲሆን፤ 540 ሚሊዮን ቶን የሚገመት የፖታሽ ክምችት አላት። የጂኦተርማል አቅሟም እስከ 10ሺ ሜጋ ዋት በላይ ማመንጨት አቅም አላት። በአሁኑ ወቅት ያላት የድንጋይ ከሰል ክምችትም ግማሽ ሚሊዮን ቶን በላይ የሚጠጋ እንደሆነ ይገመታል።

እስካሁን ድረስ በተደረገው የዳሰሳ ጥናት የተለየውን የሀገሪቱ የማዕድን ሀብት ከፍተኛ ክምችት መጠን ስንመለከትም ዘርፉ ገና ያልተነካ፣ ብዙ ሊሰራበት የሚችል እንደሆነ ያመላክታል። ይሁን እንጂ ሀገሪቱ ቀደም ባሉት ጊዜያት ለበርካታ ዓመታት ማዕድኑ እያላት በሀገር ውስጥ በማምረት መጠቀም ሳትችል ቀርታ ከውጭ ሀገር በውድ ዋጋ እያስገባች መቆየቷ ይታወሳል። በተለይ ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች፣ ለብረት፣ ለሴራሚክ፣ ለጨርቃጨርቅ እና ሌሎች ኢንዱስትሪዎችም ለኃይል ምንጭነት የሚውለውን የድንጋይ ከሰል ለማስመጣት ከፍተኛ ወጪ ስታወጣ ኖራለች። ለዚህም በየዓመት ከ300 ሚሊዮን ዶላር በላይ ስትጠየቅ እንደነበር መረጃዎች ያመላክታሉ።

ምንም እንኳን የማዕድን ሀብት ከፍተኛ ኢንቨስትመንትና መዋለ ነዋይ የሚጠይቅ እንደመሆኑ አሁን ላይ በሚፈለገው መጠን ኢንቬስት ተደርጎበት ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ማግኘት ችላለች ባይባልም ዘርፉ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራበት መሆኑ ተስፋ ሰጪ ነው። በመሆኑም ከጊዜ ወደ ጊዜ በዘርፉ ለውጦችና መሻሻሎች እየታየ ይገኛል።

ለዚህ ውጤትም አሁን ላይ ሀገሪቱ ማዕድኑ እያላት ከውጭ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የምታስገባው ማዕድን በሀገር ውስጥ በመተካት ያለመ አሰራር እየተገበረ ይገኛል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት መንግሥትም ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት ሀገሪቷ ከውጭ የምታስመጣው የማዕድን ሀብት ውጤቶች በሀገር ውስጥ ለመተካት እየተሰሩ ባሉ ሥራዎች ለውጦች እየታዩ ውጤቶች እየተመዘገቡ መጥተዋል። ለአብነትም የድንጋይ ከሰል ምርት ብንመለከት ሙሉ ለሙሉ በአገር ውስጥ የመተካት ሥራውም ተጠናክሮ ቀጥሏል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከውጭ ሀገራት የሚገባው የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ በማምረት ለመተካት በተሰሩ ሥራዎች በአሁኑ ወቅት የሲሚንቶ ኢንዱስትሪዎች ለኃይል ምንጭነት እንደዋና ግብዓትነት የሚጠቀሙት የድንጋይ ከሰል 63 በመቶ በሀገር ውስጥ በማምረት መሸፈን ተችሏል። በዚህም ምርቱን በሀገር ውስጥ በመተካት ከ120 በላይ ሚሊዮን ዶላር ዓመታዊ ወጪን ማዳን የተቻለ መሆኑን ከማዕድን ሚኒስቴር የተገኙት መረጃዎች ያመላክታሉ።



በከበሩና በጌጣጌጥ ማዕድናት ዘርፉም ከባለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ በመንግሥት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶት ሥራዎች በመሠራታቸው አበረታች ለውጦች እየታዩ መጥተዋል

እነዚህ የድንጋይ ከሰል ክምችቶችም በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች ይገኛሉ። ክምችቱ በቤንሻንጉል ጉምዝ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች ስለመኖራቸው መረጃዎች ያሳያሉ። ይህም ሀገሪቱ የድንጋይ ከሰልን በሀገር ውስጥ በማምረት ከውጭ የሚመጣውን በማስቀረት ሙሉ ለሙሉ መተካት የሚያስችል አቅም እንዳላት ማሳያ ነው።

በተመሳሳይ ሀገሪቱ እንደ ኦፓል፣ ኤመራልድ፣ ሳፋየር፣ ሩቢ፣ አጌት እና ኳርትዝ የመሳሰሉ በዓለም ላይ እጅግ ተፈላጊ የሆኑ የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት እምቅ ሀብት እንዳላትም ይታወቃል።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት አሁን ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ በከበሩና በጌጣጌጥ ማዕድናት ዘርፍ በዓመት 250 እስከ 300 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ሀብት ይንቀሳቀሳል። ይህ ሀብት በኢትዮጵያም እስከ ባለፈው ዓመት ድረስ ከሶስት እስከ አራት ሚሊዮን ዶላር ሀብት ያስገኘ ነው። ይህ የዓለምን ኢኮኖሚ እያንቀሳቀሰ የሚገኘውን ሀብት በሚገባ ለመጠቀም የሚያስችሉ ሥራዎች ከተሰራ አመርቂ ውጤቶችን ማስመዝገብ እንደሚቻል ያመላክታል።

በከበሩና በጌጣጌጥ ማዕድናት ዘርፉም ከባለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ በመንግሥት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥቶት ሥራዎች በመሥራታቸው አበረታች ለውጦች እየታዩ መጥተዋል። በተለይ ደግሞ የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት ለውጭ ገበያ በመላክ ለኢኮኖሚ ጠቀሜታ እንዲውሉ የማልማት ሥራው ተጠናክሮ ቀጥሏል።

በአሁኑ ወቅት የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት ላይ እሴት በመጨመር ለውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሪን እንዲያመጡ እየተደረገ ይገኛል። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን የሚበልጠውን ገበያ የያዙት ምንም ዓይነት እሴት ሳይጨመርባቸው በጥሬው የሚላኩት ማዕድናት ናቸው።

የዘርፉን የአምስት ዓመታት የውጭ ገበያ መረጃ ይህንኑ የሚያመላክት ነው። በአምስት ዓመታት ለውጭ ገበያ ከተላኩት የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናት 95 በመቶ ያህሉ በጥሬው (ምንም ዓይነት እሴት ሳይጨመርባቸው) እየተላኩ ሲሆን፤ ቀሪዎቹ አምስት በመቶ ያህሉ ብቻ እሴት ተጨምሮባቸው የሚላኩ መሆኑን ነው።

የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ በአንድ ወቅት ስለከበሩ ማዕድናት ሲናገሩ ሀገሪቷ በከበሩ ማዕድናት ዘርፍ የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ በማድረግ ወደ ቀጣይ ምዕራፍ እንዲያሸጋገሩ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በከበሩት ማዕድናት ዘርፍ ከ40 ያላነሱ ማዕድናት ይኖሯት እንጂ ሀብቱ በቅጡ ስላልታወቀ ጥቅም ላይ አልዋለም። ለዚህም ደግሞ ዋንኛ ምክንያት እስካሁን በዚህ ዘርፍ እውቀና ያላቸው ባለሙያዎች ስላልነበሩ ያላለቀለትና እሴት ያልተጨመረበትን የከበረ ድንጋይ ለተለያዩ ሀገራት ስናቀርብ ኖረናል ነው ያሉት ሚኒስትሩ። ይህ ደግሞ እንደ ሀገር ማግኘት የሚገባትን ዋጋ ሳናገኝ፤ በብዙ ሺዎች ቶን እየላክን ከ10 ሚሊዮን ዶላር ያልበለጠ እድገት ስናስመዘግብ ቆይተናል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ እጅግ በጣም ውድ የሆነ ኦፓል፣ ሳፋየር እና ኤምራልድ የመሳሳሉ ማዕድናት ያላት ሀገር ብትሆንም እውቀት ስለሌለን በኢንዱስትሪ ደረጃ የሚያመርቱ ተቋማት ስለሌሉ ሀብቱ በከንቱ እንዲባክን ሆኗል። በከበሩት ማዕድናት ዘርፍ ከወርቅ ባልተናነሰ ሁኔታ በቢሊዮን ዶላር ኤክስፖርት ማድረግ ትችላለች። በማዕድን ዘርፉ ዋንኛ ኤክስፖርት የሚደረገው ተደርጎ የሚቆጠረው ወርቅ ነው። ነገር ግን በደንብ ከተሰራ የአንድ ኦፓል ዋጋ ከወርቅ ዋጋ በላይ ያወጣል። በመሆኑን ዘርፉን በእውቀትና በቴክኖሎጂ ተደግፎ ሊመራ ይገባል ማለታቸው የሚታወስ ነው።

የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማትዮስ በበኩላቸው ኢትዮጵያ የተለያዩ የማዕድን ሀብቶች ያሏት ሀገር እንደመሆኗ የማዕድን ሀብቷን በማልማት የመጠቀም ሰፊ እድል ያላት መሆኑን ይገልጻሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ የመጀመሪያው ጉዳይ ሀገሪቱ ያላትን ሀብት ለይቶ በማወቅ የማዕድን ሀብቱ በየትኛው አካባቢ በምን ያህል መጠን ሊለማ ይችላል የሚለው ሥራ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። በመቀጠልም ማዕድን ሀብቱ የሚለማበት ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል።

ሀገሪቷ ከማዕድን ዘርፍ ባላት አቅም ልክ ተጠቃሚ እንድትሆን ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ነው። በተለይ ዘርፉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሰፊ የሥራ እድል መፍጠር ያስችላል። በ2016 በጀት ዓመት ስምንት ወራት አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዜጎች በዘርፉ ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ ጠቅሰው፤ በተዘዋዋሪ ደግሞ ከሰባት ሚሊዮን በላይ የሆኑ ዜጎች ከዘርፉ ተጠቃሚ እንደሆነ መናገራቸው ይታወሳል።

በተለይ በአሁኑ ወቅት ዘርፉ እንዳያንሰራራ እያደረጉ ያሉት ዋንኛ ተግዳሮቶች መካከል አንዱ ሕገወጥነት መሆኑ ይጠቀሳል። እንደሚኒስትር ዴኤታው ማብራሪያ ሕገ ወጥነት በመከላከል ረገድ ከፌዴራል እስከ ክልል ያለው ተቋማት ተቀናጅቶ እንዲሰሩ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የሚመራ ሀገራዊ የማዕድን ካውንስል ተቋቁሞ ወደ ተግባር ተገብቷል። ካውንስሉ የክልል ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ ሚኒስትሮችም የተካተቱበት ስለሆነ ከክልልና ከፌዴራል ያሉ አካላት በቅንጅት ሥራዎችን የሚሰሩበት ነው።

የማዕድን ካውንስሉ ቅንጅታዊ አሰራሮችን መከተል በማዕድን ዘርፍ ውጤት ያመጣል ተብሎ ይታሰባል ያሉ ሚኒስትር ዴኤታው፤ በዘርፉ ተንሰራፍቶ ያለውን ኮንትሮባንድ ንግድና ሕገ ወጥነት ለመቅረፍም የክልል እና የፌዴራል የጸጥታ መዋቅሩ ከፖለቲካ አመራሩ ጋር ተቀናጅቶ የሚሰራበትን እድልም የሚፈጥር ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በአጠቃላይ ሀገሪቷ በማዕድን ዘርፉ ያላት ሰፊ የመጠቀም አቅም በተወሰነ መልኩ ለማንሳት ተሞከረ እንጂ እያንዳንዱን የማዕድን በዝርዝር ብንመለከት ሰፊ ጊዜና ሰዓት ይፈጃል። አሁን ላይ እየታዩ ያሉ ጅምሮችም ተጠናክረው ቀጥለው ሀገር ከሀብቱ ተጠቃሚ መሆን እንድትችል የሁሉንም አካላት ርብርብ ይጠይቃልና በተለይም የሚመለከታቸው ሁሉ የየድርሻቸው በመወጣት ዘርፉን ማሻገር ይገባል የዝግጅት ክፍሉ መልዕክት ነው።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ሆያ ሆዬ እና እዬዬ

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽከታብ)

ምድር አረንጓዴ ባተቶ ለብሳለች። ሰማዩ ሊሄድ በቃጣው የክረምት ጭጋግ ቡራቡሬ መልኩን ይዞ ከበላይ ተሰትሯል። አደይ አበባዎች በየመስኩና በየሜዳው በላያቸው ላይ ነፍሳትን አሳፍረው ይታያሉ። አዕዋፍት በበረታና ባዘገመ ፉጨት ከአንባ ሲደመጡ መስከረም ሁሌ በመጣ ያስብላል።

ጋሽ ፍሰሃ የዘጠኝ ልጆች አባት መሆናቸው የሚያስቆጫቸው በዓል በደረሰ ሰሞን ነው። መቼም ለምን የሚል አይጠፋም.. መስከረም ከነከርሱ አፍጦ፣ እንቁጣጣሽና መስቀል ፊት ቆመው አዬዬ የማይል ካለ ዳንጎቴ ብቻ ነው።

ለዘጠኝ ልጆች አባት አዲስ ዓመት የአዲስ መከራ መምጫ እንጂ የአሮጌ ዓመት መሄጃ አይደለም። አዲስ ዓመት ውበት ያለው ላለው ከሆነ ሰነባብቷል። ለሌለው የሌለው መሆኑን ከመናገርና በጎረቤት ተድላ ከመቋመጥ ባለፈ እርባና የለውም። አዲስ ዓመት እንደስሙ የአዲስ ዓመት ጅማሮ ቢሆን ጥሩ ነበር ግን አይደለም። ከአሮጌው ዘመን ጋር የሚለዋወጠው ሽርና ክፋት አለው። ያላለቁ አበሳዎች የሚያልቁበት..

‹ዘመን መለወጫ ድሮ ቀረ› የሚል ተረት አውሪ ትውልድ እየተፈጠረ ነው። በስሙኒና በድንቡሎ ሙክት እያረደ ቀን የወጣው አያቴ ይሄን ዘመን በመጠየፍ ተወዳዳሪ የለውም። እናቴስ ብትሉ እናትና አባቷ ጋር የበላችውን እያሰበች፣ ከአባቴ ጋር በአፍላ ፍቅር የሆኑትን የዝብናኔ ጊዜ እያስታወሰች ይብላኝ ለእናንተ በስጋ ፈንታ ስጋት ለገባችሁና በስግብግብ ትውልድ አህያ ቄራ ለዋላችሁ ወደማለት ተሸጋግራለች። እኔ ምንም አልል..ሃሳቤን በእናትና በአባቴ ላይ ጥዬ ከርሴን እሞላለሁ።

ሰው እስከሆነ ጊዜ ድረስ ሃሳብ የሌለው እንስሳ ነው። አእምሯችን በምቾት አንቀላፍቶ ሰንብቶ ለራሳችን መኖር በጀመርንበት የሆነ ጊዜ ላይ ላለመውደቅ የምናደርገውን ትግል አይቶ የሚነቃ ይሆን? እንደዛ ይመስለኛል.. ሁሉም ሰው ለማለት በሚደፍር ንግግር እናገራለሁ አንቀላፍተን የምንነቃ ነን። ያስደገፉን ሲንሸራተቱና የያዙን ሲያፈገፍጉ ያን እለት ማሰብ እንጀምራለን። የእኔ ማሰቢያ ጊዜም የከንፈር ወዳጅ ይገዤ፣ ስለእሷ ሳስብና ስለአብሮነታችን ስተክዝ እንዲሁም ጥርስ ያበቀሉ ስሜን ሸሽገው አባዬ ብለው የሚጠሩኝ ልጆች ሲኖሩኝ ያን ጊዜ ነው እላለሁ።

ስጋ ስጋት የሆነበት ዘመን፣ ሰላም ቅንጦት የሆነበት ጊዜ ለትውልዱ የሥነቃል መዝገበ ቃላት ቢሆን ምን ይገርማል? እንደአባቶቹ ዘመን ከወዳጅ ዘመድ ስቆና ተጫውቶ፣ አጋርቶና ተጋርቶ ተመስጌን ብሎ የማይቀበለው ዘመን መጣ ቀረ ምን ሊበጀው? ደግሞስ በቀይ ምንጣፍ ጉዝጓዝ ላይ እንደልብ የማይሆኑለት ዘመን ምን ዘመን ሊባል?

‹እንቁጣጣሽ እንኳን መጣሽ› ለዚህ ትውልድ ምኑም ነው። በደህናው ጊዜ እነዘሪቱ ጌታሁን ዘፍነውታል። ጠሙን በሽሮ ለሚፈታ፣ አዲስ ዓመቱን በባዶ ሌማት ለሚቀበል ትውልድ የዘመን መለወጥ ምኑ ነው? ሁዳዴን ሆነ ትንሳኤ በጾመኞች ሀገር ነን.. እናም ይሄ ትውልድ በዘመን ላይ ተረት ሲያንሰው ነው።

ሽሮ ባቅሟ መችና የት ልብላ በሚል ፈሊጥ እቅድ ውስጥ ስትገባ አስባችሁታል..እናስ ዘመን መጣ ቀረ ምን ሊፈይድ? ያቺ ከቅቤ ጋር በየሰው ቤቱ የማይጠፋው፣ ያቺ የሰንደቅ ዓላማችንን ያክል በሁላችን ታሪክ ላይ የተውለበለበችው.. ያቺ የአረንጓዴ ቢጫ፣ ቀይን ያክል የምናውቃት ሽሮ የስጋን ክብር ይዛ ከቤታችን ከጠፋች ሰንብታለች። የት እንብላ በምን እንብላ የተቀየረበት ትውልድ። ከየትና ምን እንብላ ጦም ወደማደር የዘመነባት ሀገር..አዲስ ዓመት ምን ሊሠራው?

ድሮ ሽሮ የድሃ ባንዲራ ነበረች አሁን ሽሮ መካከለኛ ገቢ ላለው ማህበረሰብ ገቢ ሆናለች። ድሃው ሳይበላ በማደርና በቀን ለአንድ ጊዜ በመመገብ ሽሮ ናፋቂ..ድሮን አድናቂ ወጥቶታል። ያቺ የተቀናጣንባት..ልጅነታችንን እንደዶቃና አንቀልባ አቅፋና ሸክፋ በእሸሩሩ ቀን ያወጣችን ሽሮ ከድሃ ድሃ ወደ መካከለኛ የማህበረሰብ ክፍል ስትመነደግ ነገን ሰጋሁት። ነገስ የባለጸጎች የማትሆንበት ምን ዋስትና አላት? ወደሞጃዎች ከአሁኑ ዳዴዋን ጀምራለች..

ሙክት የሌለበት ዘመን፣ ቅርጫና ዶሮ፣ ከጠላና ጠጅ፣ ከቤት ያፈራው ጋር የሌለበት አውደዓመት፣ ዘመድ ያልመጣበት ወደዘመድ ያልተኬደበት ጉርብትና፣ ልጆች አዲስ ለብሰው ወላጆች በክት አጊጠው በሳቅ ያልዋሉበት፣ አበባየሆይ ያላሉበት..ቄጠማና ጠጅ ሳር፣ እጣንና ሰንደል ያልጨሰበት ከሰዓትና ማለዳ እውን አዲስ ዓመት ነው? ዘሪቱ ጌታሁን ያልዘፈነችበት፣ ሀመልማል ያላዜመችበት፣ ጤና ለሰጠው ሰው እድሜውን ላደለው አውዳመት ጸጋ ነው.. ስትል ማን አለሙሽ ያልተምነሸነሸችበት፣ በአስራ ሶስት ወር ጸጋ ዜማው ጥሌ ያላቀነቀነበት አውዳመት አላውቅም።

እንኳን አደረሳችሁ የሚል የወዳጅ ዘመድ መልካም ምኞት የማይሰማበት፣ የዶሮ ሽታው፣ የዳቦው መዐዛ አጥር ባልዘለለበት፣ በምነው ባልመጣ ስሜት ቤቱ መሽጎ ማግስት እስኪሆን የሚጠብቅ ጎረቤት በበዛበት ቅዱስ ዮሃነስ ትርጉም የለሽ ነው።

በዓል በሁለት ልሳን የሚገለጽ ሆያሆዬና እዬዬ ነው። ለአንዳንዱ ሆያሆዬ ለሌላው እዬዬ የሁለት ወግ ስሜት። የላመና የጣፈጠ ለሙብላት ዓመት የሚጠብቁ እንደጋሽ ፍሰሀ ያሉ ቤተሰቦች የመኖራቸውን ያክል አዲስ ዓመትን ለአዲስ ፌሽታ የሚጠብቁም ጥቂቶች አይደሉም።

ድሃ አዲስ ዓመት የለውም። የጠገበ እለት አዲስ ዓመቱ ነው። እኚህ ነፍሶች ለዘመን መቁጠሪያነት እንጂ ለተለየ ተልዕኮ አዲስ ዓመትን አይፈልጉትም። ለአንዳንዶች ካልሆነ ለብዙሃኑ አዲስ ዓመት የአዲስ መከራ መምጫ ነው ስለዚህም ብዙዎች ይፈሩታል።

ጋሽ ፍሰሃ በጥበቃ ሥራ የሚተዳደሩ የዘጠኝ ልጆች አባት ናቸው። ደም ብዛታቸውን ጨምሮ በሳይንስ ያልተረጋገጡ በሽታዎችን የሚታመሙት በአውዳመት ማግስት ነው። ደህና ሰንብተው ብቻቸውን ማውራት የሚጀምሩትና አንዳንዴም መንገድ ወድቀው በቃሬዛ ቤት የሚገቡት በበዓል ሰሞን ነው። እናስ ከትውልዱ ጋር አብረው ተረት ቢተርቱ፣ በዘመን ላይ ጥርስ ቢነክሱ ምን ይደንቃል?

ከነሐሴ አጋማሽ የቡሄ ጅራፍን ተከትሎ እስከ ጳጉሜ መዳረሻ ድረስ የእዬዬ ሰሞናቸው ነው። የዘንድሮውን በዓል በሆነ መላ ካልሆነ በጥበቃ ደሞዛቸው የሚዘልቁት አልመሰላቸውም። ስለሆነም በዓልን ታኮ ለሚመጣው የልጆቻቸው የፍላጎት ጥያቄ ከወዲሁ መላ ለማዘጋጀት ከራሳቸው ጋር ሳምንት መክረዋል። ትናንት ማታ ከሥራ ውለው ወደቤታቸው ሲገቡ በሚገርም ንቃት ነበር። ይሄን ንቃታቸውን ያየች ባለቤታቸው ወይዘሮ ይመኙሻል ከእንዴት አመሹ በፊት ‹ምነው ሥራ አልገባህም እንዴ? ስትል ከመንገድ እንደተቀበለቻቸው ያስታውሳሉ። ለሊቱን ከዚህ ብልሃታቸው ጋር አድረው ነቁ።

ማለዳ የበዓል ሰሞን ላይ የሆነ የሚገዛ ድባብ አለው። ሁሉም ነገር ውብ የሚሆነው በዓል ሰሞን ላይ መሆኑ ለኔ ብቻ ይሆን የሚገርመኝ? በሚዘምሩ ወፎች፣ በሚንጣዙ ነፍሳት፣ በለመለሙ ሳሮች፣ በአረንጓዴ ቀይ፣ በብሩህ ሰማይ፣ በዘሪቱ ጌታሁን ዜማ ታጅቦ የማይደንቅ ማለዳ ይኖር ይሆን? ካለ ለጋሽ ፍሰሃና ሽሮ ለከዳቻቸው ድሆች ይመስለኛል..


በግምት ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት ቢሆን ነው..ጋሽ ፍሰሃ ለቤተክርስቲያን መሳሚያ እና ለአንዳንድ ሁነኛ ጉዳይ ካልሆነ በማይጠቀሙበት ሀጫ ጋቢያቸው ጋር ወደቤት ሰተት አሉ። ከነጭ ጋቢያቸው ጋር ሲታዩ ከመላዕክት አንዱ ወደቤታቸው ጎራ እያለ ይመስል ነበር።

በማለዳ ከእኩዮቻቸው ጋር ተጠራርተው ለእንቁጣጣሽና ለሆያ ሆዬ ልምምድ ከወጡ አራት ልጆቻቸው በቀር አምስቱ ልጆቻቸው ዙሪያቸውን ከበው ስለሚገዛላቸው አዲስ ልብስ ሲያውኳቸው..ከከረመ መላቸው አንዱን መዘው ይሄን አሉ..‹ልጆቼ ለአዲስ ዓመት አዲስ ልብ እንጂ አዲስ ቀሚስ አያስፈልግም። በአዲስ ልብ ፈንታ አዲስ ልብስ እየገዛን ነው አሮጌነታችንን መሻር ያቃተን። በልብሳችሁ ሳይሆን በሃሳባችሁ አዲስ መሆንን ተለማመዱ። ይሄ ለሁላችሁም የበዓል ስጦታዬ ነው.. ከእኔ ለእናት ከእናተም ለልጅ ልጃችሁ የተላለፈ...። በመሻገር ቀን ላይ ይሄን አይነቱን እሳቤ ማለፍ ይጠበቅብናል..› በማለት ልጆቻቸውን በየተራ አቀፉ።

# ዓለም አቀፍ

## ቻይና በቀጣዮቹ ሶስት ዓመታት 50 ቢሊዮን ዶላር ለአፍሪካ ድጋፍ አደርጋለሁ አለች

በጋዜጣው ሪፖርተር



ሺ ዢን ፒንግ

በቤጂንግ የቻይና አፍሪካ መሪዎች ጉባዔ የተመድ ዋና ጸሀፊን አንቶኒዎ ጉቴሬዝን ጨምሮ ከ50 በላይ የሀገራት መሪዎች ተሳትፈዋል፡፡ የቻይናው ፕሬዚዳንት ሺ ፒንግ ባደረጉት የጉባዔው መክፈቻ ንግግር ቻይና እና አፍሪካ ከመቼውም ጊዜ በላይ ምርጥ ግንኙነታቸውን እያጣጣሙ ነው ብለዋል፡፡

ፕሬዚዳንቱ አክለውም ቻይና በቀጣዮቹ ሶስት ዓመታት ውስጥ 50 ቢሊዮን ዶላር ለአፍሪካ ትሰጣለች ማለታቸውን ሮይተርስ ዘግቧል፡፡ ከዚህ ውስጥም 25 ቢሊዮን ዶላሩ በብድር መልኩ ለአፍሪካ ሀገራት ይሰጣል የተባለ ሲሆን 11 ቢሊዮን ዶላሩ ደግሞ ርዳታ እንዲሁም 10 ቢሊዮን ዶላሩ ደግሞ የቻይና ኩባንያዎች ወደ አፍሪካ ሄደው ኢንቨስት እንዲያደርጉ የሚደረግ ድጋፍ እንደሚውል ተገልጿል፡፡

የገንዘብ ድጋፉ ለአንድ ሚሊዮን አፍሪካውያን የሥራ እድል እንደሚፈጥርላቸው ፕሬዚዳንቱ በመክፈቻ ንግግራቸው ላይ ጠቅሰዋል፡፡ የዓለማችን ቁጥር ሁለት ባለግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤት የሆነችው ቻይና ከአፍሪካ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላት ሲሆን ለዚህ ጉባዔ ወደ ቤጂንግ ያቀኑ ሀገራት አዳንድ የንግድ እና ኢንቨስትመንት ስምነቶችን በማድረግ ላይ ናቸው፡፡

እስካሁንም ዛምቢያ ፣ ታንዛኒያ፣ ዚምባብዌ፣ ኬንያ እና ናይጀሪያ በርካታ የንግድ እና ኢንቨስትመንት ስምምነቶችን ከቻይና ጋር ተፈራርመዋል፡፡

ታንዛኒያና ዛምቢያ የሚያስተሳስራቸውን የባቡር መሠረተ ልማት ግንባታ ከቻይና በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ ለመገንባት ሲፈራረሙ፣ ዚምባብዌ አቮካዶ ምርቶቿን ወደ ቻይና ገበያዎች መላክ የሚያስችላትን የንግድ ስምምነት መፈራረማቸው ተገልጿል፡፡

ናይጀሪያ ደግሞ የወደብ ልማት፣ ነጻ የንግድ ቀጣና እና የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶችን ለመገንባት ከቻይና ኩባንያዎች ጋር ተፈራርማለች፡፡ ዛምቢያ የታዳሽ ሃይል ኢንቨስትመንት ስትፈራረም ኬንያ ደግሞ የግብርና ምርቶቿን ወደ ቻይና አብዝታ መላክ የሚያስችላትን ከመፈራረሟ ባለፈ የባቡር መስመር ግንባታ ስምምነት እንደተፈራረመች ተገልጿል፡፡

## የእስራኤል ጦር ግብጽ ከፍልስጤም ከምትጋራው ድንበር እንደማይለቅ ኔታኒያሁ አረጋገጡ

በጋዜጣው ሪፖርተር




ቤኒያሚን ኔታኒያሁ

የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታኒያሁ የሀገራቸው ጦር ጋዛና ግብጽ ከሚጋሩት እና ስልታዊ ጠቀሜታ ካለው የፊላደልፊ ‘ኮሪደር’ እንደማይለቅ ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በእየሩሳሌም ለዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን በሰጡት መግለጫ ወደፊት በሚኖር ዘላቂ የተኩስ ማቆም ስምምነት ውስጥ በጋዛና ግብጽ ድንበር የእስራኤል ወታደሮችን ለማስፈር ሌላ አማራጭ ካለ “ለመቀበል ዝግጁ ነኝ” ካሉ በኋላ “ግን ሌላ አማራጭ ያለ አይመስለኝም” ሲሉ ተደምጠዋል።

ኔታኒያሁ በዚህ ነጻ የድንበር ቀጣና የመሳሪያ ዝውውርን ለመግታት እና ታጋቾች ወደ ሌላ ሥፍራ እንዳይወሰዱ የእስራኤል ጦር ወታደሮች መቆየት ይኖርባቸዋል ሲሉ ተከራክረዋል።

እስራኤል ከፊላደልፊ ‘ኮሪደር’ ወታደሮቿን አላስወጣም ማለቷ የተጀመረውን ዘላቂ የተኩስ አቁም ስምምነት የማደናቀፍ ሙከራ ነው ሲል ሀማስ መቃወሙን ሮይተርስ የዜና ወኪል ዘግቧል። ጨምሮም እስራኤል ላይ ጫና የማሳደሪያ ጊዜው አሁን ነው ብሏል።

ያለፈው ረቡዕ መግለጫ የሰጡት ኔታኒያሁ ወደፊት ማንኛውም ዘላቂ የተኩስ አቁም ስምምነት የሚኖር ከሆነ በፊላደልፊ ኮሪደር በኩል “ምንም ዓይነት ክፍተት” የሚተው ሊሆን አይችልም ብለዋል።

“በጽሑፍ ወይም በቃል ሳይሆን መሬት ላይ በተግባር በዚያ ኮሪደር ላይ እየሆነ ያለውን ለመከላከል የሚያስችል ሌላ አማራጭ ካለ ለመቀበል ዝገጁ ነን” ያሉት ኔታኒያሁ “ይህ ሲሆን አይታየኝም። እሱ እስከሚሆን ደግሞ በዚያ እንቆያለን” ብለዋል።

ኔታኒያሁ ደጋግመው እያሳዩት ያለው ፍላጎት በደቡባዊ ጋዛ የሀገራቸው ጦር የመውጣት ‘ቅንጣት’ ፍላጎት እንደሌለው ማረጋገጫ የሰጠ ነው። በድንበሩ የእስራኤል ጦር መቆየትን አስፈላጊነት “ቀይ መስመር’ ሲሉ ገልጸውታል።

“ሰዎችን ይህ ውሳኔ (ከድንበሩ የእስራኤል ጦር መውጣት) ስምምነቱን ያኮላሸዋል ይላሉ። እኔ ደግሞ ይህ ከሆነ እኛን ያኮላሸናል እላለሁ” ሲሉ ተናግረዋል።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# ዘመን አሻጋሪ በጎነት

**ማህሌት አብዱል**

አዲስ ዓመት ሁልጊዜም አዲስ ነው፤ ዘመን አልፎ ዘመን ቢተካም አዲስ ዓመት በመጣ ቁጥር ሁሉም የትናንቱን የጨለማ ወቅትና የመከራ ጊዜ ረስቶ ለአዲስ ነገር፤ ለአዲስ ተስፋ ልቡን አስፍቶ በተስፋ የሚጠብቅበት የመልካም ብስራት ማሳያ ነው። ብዙዎች አዲሱን ዓመት ሲቀበሉ ያሳለፉትን መጥፎ ትዝታ፤ ቁርሾና ጥላቻ ሁሉ ወደኋላ ጥለው እርስበርስ ይቅር የሚባባሉበት፤ ያለው ለሌላው ማዕዱን በማጋራትና ድጋፍ በማድረግ ፍቅሩንና ውግንናውን የሚገልፅበት በዓል በመሆኑ ሁሉም በጉጉት ይጠብቀዋል።

ኢትዮጵያውያን በችግር ጊዜ የመረዳዳትና የመደጋገፍ ባሕላቸው ዘመናትን ያስቆጠረ እንቁ የሚባል እሴት ቢሆንም ቅሉ እንደ ዘመን መለወጫ ያሉ በዓላት ወቅት ከወትሮ በተለየ መልኩ ድጋፋቸውና መረዳዳታቸው ጎልቶ የሚታይበት መሆኑ ይበልጥ ደማቅ ያደርገዋል። ይህ በዓላትን ጠብቆ የሚደረገው የመረዳዳትና የመደጋገፍ ባሕል ታዲያ ኅብረተሰቡ ጋር ብቻ የቀረ አይደለም፤ በተለይ አሁን አሁን መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት በተለያዩ ችግር ውስጥ ያሉ ዜጎችን በማስታወስ ማዕድ የማጋራትና ለበዓሉ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በመለገስ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ይገኛሉ።

በዚህ ረገድ የፋይናንስ ተቋማት እንደ ኢትዮ-ቴሌኮም ያሉ መንግስሥ ድርጅቶች በዚህ ረገድ አብነት ተደርገው የሚጠቀሱ ናቸው። ዘንድሮም የተለያዩ ተቋማት ለእነዚህ ዜጎች ያላቸውን ፍቅር በሚገልፅ መልኩ ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። መንግሥትም ዜጎቹ ያሳለፉትን ችግርና ክፉ ጊዜ ሁሉ ወደኋላ ጥለው ወደፊት አዲስ ራዕይ ሰንቀው እንዲሻገሩ ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ከእነዚህ ሥራዎች መካከልም ጳጉሜን 1 ቀን 2016 ዓ.ም የመሻገር ቀን «የመሻገር ጥሪቶች፤ የአዲስ ብርሃን ወረቶች ” በሚል የተሰየመ ሲሆን፤ ሁሉም ዜጋ አዳፋውን ጥሎ አዲስ ተስፋን ሰንቆ መጪውንና ብሩሁን አዲስ ዓመት እንዲሻገር የማድረጉ ሥራ ተጠቃሽ ነው።

በተመሳሳይ የተለያዩ የግል ተቋማት ከትርፋቸውም ሆነ ካለቸው እሴት ላይ በመቀነስ ለሌሎች በማካፈል ችግር ውስጥ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎች አዲሱን ዓመት በአዲስ ተስፋ እንዲቀበሉ የማድረግ ሥራ እያከናወኑ ይገኛሉ። በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ካሉበት ሁኔታ ለማውጣት በቋሚነት ድጋፍ ከሚያደርጉ የፋይናንስ ተቋማት መካከል ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ተጠቃሽ ነው። ባንኩ የ2017 ዓ.ም ዘመን መለዋጫ በዓልን ምክንያት በማድረግ ከሰሞኑ ለልብ ህሙማን ሕፃናት ማዕከል የበዓል ማክበሪያ 200 ሺ ብር ድጋፍ አድርጓል።

የንብ ኢንተርናሽናል ባንክ ዋና ሥራ አስፈፃሚ እመቤት መለሰ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ባንኩ የ25ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን ለማክበር በዝግጅት ላይ የሚገኝ ሲሆን፤ በዚህ ጊዜ በተቋቋመለት ዋነኛ ተግባር መስክ አመርቂ ውጤት በማስመዝገብ እንደ ሀገርም እንደ ከተማም የተለያዩ አበርክቶዎችን እያኖረ ይገኛል። ከዚሁ ቀዳሚ ተግባሩ ባልተናነሰ በተለያዩ ሀገራዊ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ እገዛው በተፈለገበት ጊዜ ሁሉ አለሁ ባይነቱን በተግባር የሚያሳይ ነው።

ለባንኩ ለውጥ የሚያመጡ የበጎ አድራጎት ማህበራዊ አጀንዳዎች ትልቅ አጋጣሚዎች መሆናቸውን ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ ጠቅሰው፤ «ከዚህ በርካታ ኢትዮጵያውያንና ልበ ቀና ሰዎች በሙሉ እጃቸውን ከሚዘረጉለት ማዕከል ጋር ለበርካታ ዓመታት የቆየ ግንኙነት አለው» ይላሉ። ማዕከሉ አሁን የህክምና አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝበት ማዕከል ከ16 ዓመት በፊት በሚገነባበት ወቅት ድጋፍ ካደረጉ ተቋማት መካከል አንዱ ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ መሆኑንም አመልክተዋል።

ማዕከሉ አሁን ላይ ለታካሚዎች አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝበት የልብ አልትራሳውንድ ምርምር መስጫ ማሽን ከአራት ዓመታት በፊት ከሶስት ሚሊዮን ብር በላይ በማውጣት ለማዕከሉ ድጋፍ ማድረጉንም ያስረዳሉ። በዚህ ድጋፍ በየወሩ በአማካይ ከ700 በላይ የልብ ህሙማን ህፃናት የነፃ የምርመራ አገልግሎት እያገኙ መሆኑንም ይጠቅሳሉ። በርካታ የባንኩ ሠራተኞችም በአሁኑ ወቅት በግላቸው የማዕከሉ ደጋፊ



ዶክተር እመቤት መለሰ



አቶ ህሩይ አሊ

ሆነው አጋርነታቸውን እያሳዩ ሲሆን በደጋፊ አባልነትና በአጭር የጽሑፍ መልዕክት የገቢ ማሰባሰቢያ መንገድ ድጋፍ እያደረጉ ስለመሆኑም ነው ያብራሩት።

ባንኩ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን ከመወጣት አንፃር ሰፊ የኢንቨስትመንት ሥራ እንደሚሰራ ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ ይናገራሉ። በተለይም በማህበረሰቡ ሕይወት ላይ አወንታዊ ሚና ሊጫወቱ በሚችሉ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ የሕዝብ አጋርነቱን በተጨባጭ ማረጋገጥ መቻሉን ያስረዳሉ። ከእነዚህ መካከል ለስፖርቱ ዘርፍ እድገት ከፍተኛ ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን ጠቅሰው፤ «ኬሮድ ኢትዮጵያ የተባለና የኢትዮጵያ ታላቅ ሯጫን ያቀፈ ማህበርን እንዲሁም ከዚህ ቀደም በሙያቸው ሀገራቸውን ሕዝባቸውን ሲያገለግሉ የነበሩ አሁን ላይ ደግሞ ችግር ውስጥ የወደቁ የኪነ-ጥበብ ሰዎችን ከፍተኛ በጀት መድበን ድጋፍ እያደረግን ነው» ይላሉ።

በተጨማሪ እንደ ሜሪጆይ፣ የልብ ህሙማን ሕፃናት ማዕከል፤ የአዛውንቶችን ማዕከላት ከሚደግፉቸው ተቋማት መካከል ተጠቃሽ መሆናቸውን ተናግረው፤ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ችግኝ በመትከልና የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ በልማቱም ዘርፍ ተሳትፎውን አስመስክሯል። እንዲሁም አሁን ላይ እየተከናወነ ባለው የኮሪደር ልማትም የበኩሉን አስተዋጽኦ እየተወጣ ስለመሆኑ ይገልፃሉ። «አሁን ላይ በከተማችን የሚታዩት ስማርት ፖሎች ላይ ከአራት ሚሊዮን ብር በላይ ኢንቨስት አድርገናል» ይላሉ።

ይህም እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ የፋይናንስ ተቋማት ያለበትን ማህበራዊ ኃላፊነት ለመወጣት ከሚሰራቸው ሥራዎች መካከል ዋነኛው መሆኑን ያስረዳሉ። ከዚህም ባሻገር ከማይክሮ ፋይናንስ ድርጅቶች ጋር በመሆን ኃላፊነቶችን ለመወጣት ከተያዙ በጀቶች ላይ የሥራ ፈጠራ ሃሳብ ኖሯቸው በፋይናንስ እጥረት ቤታቸው ቁጭ ያሉ ሥራ ፈጣሪዎችንም የማይመለስ ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን ይገልፃሉ። ባንኩ ችግር ውስጥ ያሉ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች እያደረገ ያለው ድጋፍ ወደፊትም ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም አስገንዝበዋል።

አቶ ህሩይ አሊ የኢትዮጵያ የልብ ህሙማን ሕፃነት መርጃ ማዕከል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ናቸው። እንደ እርሳቸው ማብራሪያ ማዕከሉ ከ34 ዓመት በፊት የተቋቋመ ሲሆን የመጀመሪያዎቹ 20 ዓመታት ንግሥት ዘውዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል ውስጥ የልብ ህሙማን ሕፃናትን ወደ ተለያዩ ሀገራት በመላክ ህክምና እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ አከናውኗል። ይሁንና በረጅም ጊዜ ዓላማው አራት እቅዶች የነበሩት ሲሆን፤ እነዚህም የራሱን ሆስፒታል መገንባት፣ መሳሪያዎችና የሰው ኃይል ማሟላት እንዲሁም ዘላቂነቱን ማረጋገጥ ናቸው። በዚህም መሠረት ከ16 ዓመት በፊት «አንድ ብር ለአንድ ልብ» በሚል በተዘጋጀው የገቢ ማሰባሰቢያ ዘመቻ ከፍተኛ ገንዘብ ማሰባሰብ በመቻሉ የራሱን ሆስፒታል እውን ማድረግ ቻለ።

ጎን ለጎንም መሳሪያውን በማሟላት ወደ ውጭ በመላክ የሚደረገውን የህክምና አገልግሎት ሀገር ውስጥ ማከናወን መቻሉን ዋና ሥራ አስፈፃሚው ያስረዳሉ። «ሆስፒታሉ ሥራ ከጀመረበት ከዛሬ 16 ዓመት ጀምሮ ከስድስት ሺ በላይ የልብ ህሙማንን በነፃ ማከም ችሏል» ይላሉ። ይሁንና የመጀመሪያዎቹን ስድስት ዓመታት ከውጭ በሚመጡ ባለሙያዎች ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ ዘላቂነት ለማምጣት የማያስችል እንደነበረ ይገልፃሉ። በመሆኑም በራስ አቅም ህክምናውን መስጠት ያስችል ዘንደ ሐኪሞችን ወደ ውጭ በመላክ በልብ ህክምና ዘርፍ ሰልጥነው እንዲመጡ በማድረግ ላለፉት አስር ዓመታት ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ በኢትዮጵውያን ብቻ ህክምናውን መስጠት መቻሉን ነው ያብራሩት።

ከእነዚህም መካከል ከዓመታት በፊት የልብ ህመምተኛ የነበረና ታክሞ አሁን ደግሞ የልብ ሐኪም በመሆን ማዕከሉን እየደገፈ ያለ ወጣት መኖሩን ይጠቅሳሉ። በተመሳሳይ በፋርማሲስትና በሌሎችም ሙያዎች ተሰማርተው ተቋሙንም ሆነ ሀገራቸውን በመደገፍ ላይ የሚገኙ በርካታ ወጣቶች መኖራቸውን አመልክተው ይህም የሆነው በመላው በጎ አድራጊ ኢትዮጵያውያን ድጋፍ መሆኑን ያስገነዝባሉ። «ትውልዱ ካለበት ችግር ተላቆ አምራች ዜጋ የማድረግን ያህል ትልቅ ሥራ የለም፤ ማዕከሉም ሆነ ህሙማኑ ካሰቡበት ለመድረስ የበጎዎችን ድጋፍ ይሻሉ፤ ለዚህም ነው እዚህ መድረስ የተቻለው» ይላሉ።

የልብ ህክምና ሥራ በአንድ ጊዜ ተሟልቶ የሚያበቃ አለመሆኑን ዋና ሥራ አስፈፃሚው ገልፀው፤ በተለይም የሰው ኃይሉንና መሳሪያ የማሟላት ጉዳይ ቀጣይነት ያለው ሥራ የሚሻ ስለመሆኑ ይናገራሉ። ይህ መደረጉ ደግሞ በእየለቱ የህክምና አገልግሎቱን ለህፃናቱ ለመስጠት እንዲቻል መሆኑን አስረድተው፤ ለዚህም የፋይናንስ አቅም ውስንነት ፈታኝ እንደሆነ ያመለክታሉ። «በእነዚህ ዓመታት ማዕከሉ የሚሰጠውን የህክምና አገልግሎት እንዲቀጥል መንግሥታዊ ድርጅቶች፣ የፋይናንስ ተቋማትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ሀገር በቀል የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል» የሚሉት አቶ ህሩይ፤ በተለይ ማዕከሉ ምንም ዓይነት የበጀት ድጎማ የማይደረግበት በመሆኑ ለጋሾች የሚያደርጉለት ድጋፍ ህልውና ለማስቀጠል እንዳስቻለው ያስገነዝባሉ።

ማዕከሉ ራሱን ችሎ እንዲቆም ለረጅም ጊዜ ድጋፍ ሲያደርጉ ከነበሩ የፋይናንስ ተቋማት መካከልም አንዱ የንብ ባንክ ዋነኛው እንደሆነ ዋና ሥራ አስፈፃሚው ያስረዳሉ። «ሆስፒታሉ ሥራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያልተቋረጠ ድጋፍ ሲያደርግልን ቆይቷል» ይላሉ። ማዕከሉ በእነዚህ ዓመታት ለስድስት ሺ ሕፃናት ህክምና መስጠት ቢችልም ከችግሩ ስፋት አንፃር ገና ብዙ መሥራት የሚያስፈልግ መሆኑን ይጠቅሳሉ። «የሌሎቹን ሆስፒታሎች ሳንጨምር በእኛ ሆስፒታል ብቻ ከሰባት ሺ በላይ ሕፃናት ወረፋ በመጠበቅ ላይ ይገኛሉ፤ ይህም የሚያሳየው ምንም እንኳን ስንታገዝ ብንቆይም ከችግሩ ጋር ስናነፃፀረው ገና ብዙ መሥራት እንደሚጠበቅብን ነው፤ አሁንም በፍላጎትና በአገልግሎቱ መካከል ሰፊ ልዩነት አለ» ሲሉም ያብራራሉ።

በመሆኑም እንደ ንብ ባንክ ያሉ የፋይናንስ ተቋማት በዓልን አስመልክተው በሚያዘጋጁቸው መርሃ ግብሮች ሁሉ ወረፋ በመጠባበቅ ላይ ያሉ የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልዶችን በማሰብ ሊደገፍ እንደሚገባም ይናገራሉ። «እርዳታ የአንድ ጊዜ ብቻ የሚያቆም አይደለም፤ ችግሩ ሰፊ እንደመሆኑ ሁላችንም በያለንበት ልንደገፍ ይገባል» ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል። በዚህ ረገድ በተለይ ኢትዮ-ቴሌኮም ባለፉት ስድስት ዓመታት በአጭር የስልክ መልዕክት ኅብረተሰቡን ለመድረስና በየጊዜው አቅሙን እንዲያሳድግ በማድረግ ረገድ የማይተካ ሚና እየተጫወተ ስለመሆኑ አብነት አድርገው ይጠቅሳሉ።

ንብ ባንክ ያደረገው ድጋፍ ከባንኩ ባሻገር በርካታ የዘርፉ ተዋናዮችንም ኅብረተሰቡንም ጭምር የሚያነቃቃ መሆኑን ያነሱት። በተለይ የፋይናንስ ተቋማት ትርፍ የሚያገኙት ከኅብረተሰቡ በመሆኑ፤ ኅብረተሰቡ ጤነኛ በሆነ ቁጥር የተሻለ ደንበኛ ማግኘት የሚችሉ መሆኑን ተረድተው ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። «ሁልጊዜ ከትርፍ አንስቶ መስጠትን ብቻ ሳይሆን እነዚህ ልጆች የእነሱም ኃላፊነት መሆናቸውን ተገንዝበው ልክ ምርታቸውን ለኅብረተሰቡ እንደሚያቀርቡት ሁሉ ቀጣይነት ባለው መልኩ ለልብ ህሙማን ድጋፍ በማድረግ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል» ይላሉ። የልብ ህሙማን እንደማንኛውም ዜጋ ከታከሙ በኋላ አምራች ዜጋ መሆኑን ኅብረተሰቡም በማዕከሉ እየተሰራ ያለውን ሥራ በመጎብኘትና ድጋፍ በማድረግ አጋርነቱን እንዲያረጋግጥ፤ የበርካታ እናቶችንም እንባ እንዲያብሱ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

ዝግጅት ክፍሉም የማዕከሉን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሃሳብ ይጋራል፤ በተለይም በተለያዩ ችግር ውስጥ ያሉ ዜጎች አዲሱን ዓመት በተስፋና በሃሴት እንዲሁም በሙሉ ጤንነት ያከብሩት ዘንድ ዘመን አሻጋሪ የሆነ በጎነትና ፍቅር ልንለግሳቸው ይገባል በማለት ለማስገንዘብ ይወዳል።

# ስፖርት





## የዋሊያዎቹ የአፍሪካ ዋንጫ የማጣሪያ ጉዞ ነጥብ በመጋራት ተጀምሯል

**ዓለማየሁ ግዛው**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን እአአ በ2025 በሰሜን አፍሪካዊቷ ሀገር ሞሮኮ አስተናጋጅነት ለሚካሄደው የአፍሪካ ዋንጫ የምድቡን የመጀመሪያ የማጣሪያ ጨዋታ ከሜዳ ውጭ አድርጎ በአቻ ውጤት ተለያይቷል። ቡድኑ ከታንዛኒያ አቻው ጋር የመጀመሪያውን ጨዋታ ያለ ግብ በመለያየት የአፍሪካ ዋንጫ ጉዞውን ጀምሯል።

በ35ኛው የአፍሪካ ዋንጫ የምድብ ማጣሪያ ጨዋታዎች በምድብ 8 የተደለደለችው ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የምድብ ጨዋታ ከትላንት በስቲያ ነሐሴ 28/2016 ዓ.ም ከሜዳዋ ውጭ አድርጋለች። በታንዛኒያ ዳሬ ሰላም ቤንጃሚን ምካምፓ ስታድየም በተካሄደው ግጥሚያ 0 ለ 0 በሆነ አቻ ውጤት ተለያይታለች። ቡድኑ ለማጣሪያው በሀገር ቤት ከ15 ቀናት በላይ ዝግጅቱን ሲያደርግ ቢቆይም፣ በጉዳት እና በተጫዋቾች አካል ብቃት መውረድ እንደፈለገ አልተንቀሳቀሰም። አሁንም የግብ ማስቆጠር ችግሩ ያልተቀረፈው ቡድኑ የአቡበከር ናስር እና አቤል ያለው አለመኖር የአጥቂ መስመሩ እንዲሳሳና የግብ እድሎች እንዳይፈጥር አድርጓል።

በመጀመሪያው ጨዋታ ብልጫ ወስዶ ሶስት ነጥብ በማሳካት ለቀጣይ ጨዋታ የሥነ-ልቦና ስንቅ የሚይዝበትን እድልም ሳይጠቀምበት ቀርቷል። ምንም እንኳን የአሰልጣኝ ገብረመድህን ኃይሌ ቡድናቸው ተጭኖ ለመጫወት ወደ ሜዳ እንደሚገባ አስቀድሞ ቢገልጹም ወደ ተቀራኒ ሜዳ ሰብሮ የመግባት እንቅስቃሴ እምብዛም አልታየም። በኳስ ቅብብል ከታንዛኒያ ብሔራዊ ቡድን የተሻለ ቢመስልም ተቃራኒ ቡድን ላይ ጫና የማይፈጥርና ትርጉም አልባ ቅብብሎች በማድረግ ያለ ሶስት ነጥብ ከሜዳ ወጥቷል። የቡድኑ የቅንጅት እና የፈጠራ ችግሮች ጎልቶ የታዩና የግል እድሎች ብዙም ያልተፈጠሩበት የመጀመሪያ ጨዋታም ነው። አሰልጣኙ አሁንም የጨራሽ አጥቂ (9 ቁጥር) እጥረት እንዳለ ቢጠቅሱም ቡድኑ የሚያስቆጭ የጎል ሙከራ አላደረገም።



**ዋልያዎቹ በአፍሪካ ዋንጫ የመጀመሪያ ጨዋታ ከታንዛኒያ ጋር 0ለ0 ተለያይተዋል፣**

ቡድኑ በኳስ ቁጥጥር የተሻለ ቢሆንም የተቃራኒ ቡድን የግል ክፍል ሰብሮ ከመግባት አንጻር ከፍተኛ የሆነ ችግር ታይቶበታል። በመሃልና በሁለቱ መስመሮች ሰብሮ ለመግባት አልፎ አልፎ የሚደረጉ ሙከራዎችም በቀላሉ በታንዛኒያ ተጫዋቾች ከሽፎ ወደ ውጤት ሳይቀየር ቀርቷል። ዋልያዎቹ በጨዋታው ትርጉም አልባ የኳስ ቅብብሎችን ያለ ተጋጣሚ ጫና ሲያደርጉ፤ በአንጻሩ የታንዛኒያ ብሔራዊ ቡድን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ፈጣን ሽግግሮችን በማድረግ አደገኛ ሙከራ ለማድረግ ጥረት አድርገዋል። ከኳስ ጋራ ምቾት የማይሰማቸው ተጫዋቾች መኖራቸውና ሽመልስን በፈጠራው ረገድ የሚተካ ተጫዋች አለመኖሩ ብሔራዊ ቡድኑን አሁንም ከበፊቱ የበለጠ ዋጋ እንዲከፍል እያደረገውም ይገኛል።

ዋሊያዎቹ ምንም እንኳን የሜዳቸውን ጨዋታዎች ከሀገር ውጭ ለማድረግ ቢገደዱም መሠረታዊ የሆኑ የቡድኑን ቴክኒካልና ታክቲካል ችግሮች ተረድቶ መፍታት የአሰልጣኙ ኃላፊነት ይሆናል። ቡድኑ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎችን ጨምሮ ባለፉት ዘጠኝ ጨዋታዎች ማሸነፍ አልቻለም። በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታዎች ድል ከተቀዳጀ ደግሞ የአሁኑን ጨምሮ ስድስት ጨዋታዎች አልፈውታል። ብሔራዊ ቡድኑ ለመጨረሻ ጊዜ በአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ያሸነፈው የግብጽ ብሔራዊ ቡድንን ነበር። በ2025ቱ የሞሮኮ አፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያም የውጤት ቀውሱ በመጀመሪያ ጨዋታ የቀጠለ ሲሆን ቡድኑ ወደ አፍሪካ ዋንጫ ተሳትፎ ለመመለስ ለሚያደርገው ጉዞ ቀጣይ የሚደረጉ ጨዋታዎች ላይ የሚያሳካው ውጤት ይጠበቃል።

አሰልጣኝ ገብረመድህን ኃይሌ ከጨዋታው መጠናቀቅ በኋላ በሰጡት አስተያየት ጨዋታው ጠንካራ እንደሆነና ለማሸነፍ ጥረት ማድረጋቸውን ገልጸዋል። ቡድናቸው በመጀመሪያ አጋማሽ ጥሩ እንቅስቃሴ በማድረጉ ማሸነፍ እንደሚገባውም ጠቅሰዋል። ታንዛኒያዎች በሜዳና ደጋፊዎቻቸው ፊት እንደመጫወታቸው ጠንካራ ተፎካካሪ ሆኖ ነው ቀርበዋል። በጨዋታው ሂደት ወደ ተቃራኒ ቡድን ግብ ክልል የመድረስ ችግር እንዳልነበረበት ጥሩ የሆነ 9 ቁጥር ተጨዋች ባለመኖሩ የአጨራረስ ችግር እንዳለበት በመጥቀስ አነጋጋሪውን አስተያየት ደግመውታል። ሃሰተኛ ዘጠኝ ቁጥርን በመጠቀም እንደ ቡድን ለመጫዋት ጥረት መደረጉን እና በኢትዮጵያ አሁንም የውጤት መጥፋት ችግር መኖሩን አምኖ ለመፍታት እየተሰራ እንደሆነም አክለዋል።

ዋልያዎቹ ከቀናት እረፍት በኋላ ሁለተኛውን እና የሜዳቸውን የመጀመሪያ የአፍሪካ ዋንጫ ማጣሪያ ጨዋታቸውን ታንዛኒያ ዳሬሰላም በሚገኘው ቤንጃሚን ምካፓ ስታድየም ሰኞ ጳጉሜን 4 ከዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ጋር የሚያደርጉ ይሆናል። ብሔራዊ ቡድኑ ጠንካራ ዝግጅት በማድረግ ከሁለተኛው የምድብ ማጣሪያ ጨዋታ ነጥብ ይዞ ወደ ሀገሩ እንደሚመለስም ይጠበቃል።

ሁሉም ቡድኖች ለ2025 የአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ለማለፍ የምድብ ማጣሪያ ጨዋታቸውን በሜዳና ከሜዳ ውጭ ያካሂዳሉ። በ12 ምድቦች 48 የአፍሪካ ሀገራት ለ35ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ለማለፍ በሚያደርጉት ጨዋታዎች ኢትዮጵያ በምድብ 8 ተደልድላለች። ታንዛኒያ፣ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ እና ጊኒ ከኢትዮጵያ ጋር የተደለደሉ ሀገራት ናቸው። 35ኛ የአፍሪካ ዋንጫ በሞሮኮ አስተጋጅነት የሚካሄድ ሲሆን አዘጋጇን ሀገር ጨምሮ ከየምድቡ አንደኛና ሁለተኛ ሆነው የሚያጠናቅቁ 24 ሀገራትን በማሳተፍ ይካሄዳል።

## የጨረታ ማስታወቂያ

### የጨረታ ቁጥር ብ/ግ/ጨ/0005/2017

ፀደይ ባንክ አ.ማ የፅህፈት መሳሪያዎችና የፅዳት እቃዎች ግዥ ለመፈጸም ፈቃድ ያላቸውን ተጫራቾች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በታች የቀረበውን መስፈርት የሚያሟላ ማንኛውም በዘርፉ የተሰማራ ድርጅት /ነጋዴ/ መወዳደር የሚችል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

1. የታደሰ ንግድ ፈቃድ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምስክር ወረቀት የግብር መከፈያ ሰርተፊኬት የታክስ ክሊራንስና ብቃት ማረጋገጫ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
2. የጨረታ ማስከበሪያ የአጠቃላይ ዋጋውን 2% ሲፒኦ /CPO/ ወይም በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ጋራንቲ የ90 ቀን በፀደይ ባንክ አ.ማ ማሰራት ይኖርባቸዋል ፡፡
3. በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ከጳጉሜ 1 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 10 ቀን 2017 ዓ.ም ባሉት የስራ ቀኖች ማለትም ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት እስከ 6:00 ሰዓት እና ከሰዓት በኋላ ከ7:00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 11:00 ሰዓት እንዲሁም ቅዳሜ ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት እስከ 6:00 ሰዓት የማይመለስ አምስት መቶ ብር /500.00/ ፀደይ ባንክ ለገሀር ቅርንጫፍ ወለል ላይ በመክፈል 7ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 704 ከግዥ ክፍል ሰነዱን መውሰድ ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን የጨረታ ሰነድ በሰም በታሸገ ፖስታ እስከ መስከረም 10 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ድረስ አዲስ አበባ ለገሀር አመልድ ህንፃ በሚገኘው ፀደይ ባንክ ዋና መ/ቤት 7ተኛ ፎቅ ግዥና ውል አስተዳደር ቢሮ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ጨረታው በዚሁ ዕለት በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከጠዋቱ 4፡30 ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በመስሪያ ቤቱ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ይከፈታል፡፡
5. ባንኩ በጨረታ ከወጣው ብዛት ላይ 50 ፐርሰንት መጨመርም ሆነ መቀነስ መብቱ የተጠበቀ ነው።
6. የጨረታው መዝጊያ ሰዓት ካለፈ በኋላ የሚመጣ ማንኛውም የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረዉም፡፡
7. ባንኩ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

አዲስ አበባ ለገሃር ስልክ ቁጥር 0115583187/0115581699

**ፀደይ ባንክ አ.ማ**

## ኦሮሚያ

ከሳሽ የኦሮሚያጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ደቡብ ምድብ ችሎት እና ተከሳሽ ጉዩ አብዱባ ( 8 ሰዎች) መካከል ስላለው የሙስና ወንጀል ክርክር አስመልክቶ 7ተኛ ተከሳሽ ዋከሎ ቱኬ ዋሪዎ 8ኛ ሀሊሞ አብዱላሂ አሊ የተባሉ መከሰሳቸውን አውቀው በቀጠሮ ቀን 3/01/2017 በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደቡብ ምድብ ችሎት በ5፡00 ሰዓት ቀርበው እንዲከራከሩ ታዟል፡፡

**በኦሮሚያ ጠቅሳይ ፍርድ ቤት የደቡብ ምድብ ችሎት የወንጀል ችሎት**

የሠሌዳ ቁጥር ኮድ ልዩ 1-1041 ኦሮ የሆነ ሊብሬ ጠፍቶብኛል ብለው ገደብ ዩኒየን የገ/ህ/ሥ/ማህበር በ29/12/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ሊብሬውን በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ ካላቀረበ መ/ቤቱ ለባለንብረቱ ሌላ ተለጭ ሊብሬ የሚሰጥ መሆኑን ያስታውቃል፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የምዕራብ አርሲ ዞን ትራንስፖርት ኤጀንሲ**
**የተሽከርካሪ የሥራ ሂደት**

የሠሌዳ ቁጥር ኮድ ልዩ 1-1040 ኦሮ የሆነ ሊብሬ ጠፍቶብኛል ብለው ገደብ ዩኒየን የገ/ህ/ሥ/ማህበር በ29/12/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት ሊብሬው በማንኛውም ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ ካላቀረበ መ/ቤቱ ለባለንብረቱ ሌላ ተለጭ ሊብሬ የሚሰጥ መሆኑን ያስታውቃል፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የምዕራብ አርሲ ዞን ትራንስፖርት ኤጀንሲ**
**የተሽከርካሪ የሥራ ሂደት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ኢብራሂም ኑርአህመድ መሀመድ የሠሌዳ ቁጥር አአ 03-01-41446 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JALK6A13877100336 ሞዴል FSR የሞተር ቁጥር 6HH1-419964 የሊብሬ ቁጥር 183995/103059/275784 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው 28/12/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፤ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርኮሪና ተሽከርኮሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን**
**የየካ ቅ/ጽ/ቤት**